# ሃይማኖታዊ
# እንክርዳድ

ቅጽ ፩



ቴዎድሮስ ደመላሽ

# ሃይማኖታዊ

# እንክርዳድ

## ቅጽ ፩

ቴዎድሮስ ደመላሽ
ዐዲስ አበባ

© ቴዎድሮስ ደመላሽ
የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው፡፡
All right reserved

ግንቦት 2012 ዓመተ ምሕረት

**የአዘጋጁ አድራሻ**

ስልክ +251 94 66 57 513
የመልእክት ሳጥን ቁጥር 29783 ዐዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
E-mail: tewoderosdemelash@gmail.com
Facebook: www.facebook.com/tewoderodemelash

# ምስጋና

«ለወደደን ከኀጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥ መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን» (ራእይ 1፥5-6)፡፡

ይህን መጽሐፍ የማዘጋጀት ሐሳብ አልነበረኝም፤ ለቴሌግራምና ለፌስ ቡክ አጠር አጠር ያለ ጽሑፍ አዘጋጅቼ ሳስነብብ «መልስ አለን» እያሉ ብቅ ብቅ ያሉ አንዳንዶች ድርሳነ ኢያቄም ወሐናን በደንብ እንድመለከተውና ሰፋ ያለ ሥራ እንድሠራ ምክንያት ሆነውኛል፡፡ ስለዚህ እነዚህ «በሁሉም ነገር ላይ መልስ አለን» በሚል በተተነፈሰው ነገር ላይ ሐሳብ የሚያቀርቡትን ሰዎች ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ብቻ ሳይሆን በብዙ ነገር ከጎኔ ያለው ሙሴ ክንደያን የሰጠኝ ጌታ ይመስገን!! ወንድሜ ሙሴ እግዚአብሔር አምላክ አንተንና የአንተ የሆነውን ሁሉ ይባርክህ!!

ማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን ከሰጠኝ ወገኖች ውስጥ ማስተዋል አስማረን ያህል «አለሁልህ» ያለኝ የለም!!! ማስተዋሌ ምንም እንኳ ያለ እኅት ባድግም የእኅትን ፍቅር በአንቺ አይቻለሁ፤ ከአንቺም አግኝቻለሁ፡፡ ማስተዋሌ ዘርሽ ይባረክ!! ጌታዬ የልብሽን መሻት ይሙላልሽ!!!

እኅቴ አባይነሽ ቅባቱ ከዚህ በፊት ከምሥራቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ ያገኘቻቸውን መረጃዎች «እስኪ ተመልከታቸው» በሚል በማቀበል ከጎኔ መሆኗን ከማሳየቷም በላይ አሁን ደግሞ ከአቅሟ በላይ የሆነ ድጋፍ በማድርግ አጋርነቷን በማሳየት ላይ ያለች እኅት ነች፡፡ አባይዬ እግዚአብሔር አምላክ በጉድለትሽ ይቁምና አለሁ ይበልሽ!!!

መጽሐፉን አዘጋጅቼ ከጨረስኩ በኋላ የራሱን ሥራ ወደ ጎን አድርጎ የእኔን ሥራ በማረምና በማስተካከል የተጋውን ወንድሜን ባዩ ታደሰ እርዳቸውን እግዚአብሔር ይስጥልኝ!!! እጆችህ ይባረኩ እላለሁ!!!

# ማውጫ

መግቢያ ..... 7
ጳጋና ጽድቅ በሐና ተሰጠን ..... 9
ሕዝቅኤል ያያቸው ዐጽሞች ለሐና የሚመሰክሩ ናቸው ..... 10
አኗኗሯ ከጥንት የሆነ ..... 12
ሔዋን ትሰግድልሻለች ..... 13
ጥቅስ ማጣመም ..... 17
ሕይወታችን ማርያም ናት ..... 19
ማርያም መባል በለምጽ ያስመታል! ..... 20
በእንቁላሉ ያልተቀጣው ..... 24
ወደ በሬ አሳደገው ..... 25
የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ..... 27
ስማችን በዓለም ለምን አልታወቀም? ..... 29
የምልጃው ሰንሰለት ..... 32
ነፍስን ከባሕር የምታሻግረዋ ሐና ..... 34
የጻፈ ያስጻፈ... ..... 35
ተራሮች ኅብስት ባሕሩም ወተትና ማር ሆኑ ..... 37
የማርያም ንጸሕና ..... 39
ከሴቶች ይልቅ ምስጋናሽ ይብዛ ..... 41
የመለኮት ሥጋ የተዋሐዳት ..... 42
ከሴቶች ተለይታ ብፅዕት ናት ..... 43
የማያልቅ ሕይወት በኅብስትና በውሃ ..... 44
ወደ እርሷ ለምኑ! ..... 46
በተባረከች ልጇ ቀኝ ..... 48

«የውዳሴና የምስጋና እጅ መንሻ» ይገባታል ........ 49
የፈጣሪን ለፍጡር ........ 50
መንግሥተ ሰማያት ለመግባት... ........ 52
ስሙን በማይጠፋ ብርሃናዊ ቀለም ይጻፈው ........ 53
የአዳም መድኀኒት «ሐና»? ........ 54
እስከ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም የሚመሰገን ስም ........ 55
ትንቢተ ሐና ........ 56
ማጠቃለያ ........ 59

የመጽሐፉ ርዕስ ማብራሪያ

ለመጽሐፉ ይህ ርዕስ የተሰጠው ጌታችን «ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ» (ማቴዎስ 13÷25) በሚል ያቀረበውን ትምህርት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በዚህ የጌታችን ንግግር ውስጥ የሚታየው ነገር በሙሉ በቤተ ክርስቲያናችን ሆኗል ብለን እናምናለን፡፡ በምሳሌው ላይ «ጠላቱ» ተብሎ የተገለጸው ክፉው ቤተ ክርስቲያናችንን ወደ ተሳሳተ ትምህርት የከተታት እንክርዳድ የሆኑትን ትምህርቶች በአዋልድ መጻሕፍት ሽፋን ወደ ቤተ ክርስቲያን በማስገባት ነው፡፡ በመሆኑም ወገኖች እንክርዳድ ከሆነው ትምህርት ተለይተው ወደ ስንዴው ጠጋ እንዲሉ ስንዴውንና እንክርዳዱን ለይቶ ማሳየት በማስፈለጉ ይህ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ እንክርዳዱን መንቀል ሳይሆን አንባቢው እንክርዳዱንና ስንዴውን ለይቶ እንዲመለከት መጣር ነው፡፡ ስንዴውን በአግባቡ ይዞ እንክርዳዱን ከራሱ ሕይወት ማስወገድ የአንባቢው ተግባር ነው፡፡

# መግቢያ

ተስፋ ሚካኤል[1] ነው የጻፈኝ የሚለው «ድርሳነ ኢያቄም ወሐና»፤ የቅድስት ማርያም ወላጆች ናቸው ተብለው የሚታመኑትን የኢያቄምንና የሐናን ታሪክ፣ የቅድስት ማርያምን ልደትና ሐና ማርያምን ጸንሳ ሳለ ተከናወነ የሚለውን ታሪክ ያስነብባል፡፡[2]

መጽሐፉ በመግቢያው ላይ «በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስውር የሚታወቀውን የእመቤታችንንና የወላጆቿን ማንነት በግልጽ የሚያስረዳ» መጽሐፍ መሆኑን ይናገራል፡፡[3] የታሪኩ ምንጭ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ እንዳይነሣበትም፤

> እንደ ድርሳነ ሐና ወኢያቄም ያሉ መጻሕፍትን አዋልድ /ልጆች/ የምንላቸውም ከዐሥራው መጻሕፍት (ከመጽሐፍ ቅዱስ) ሐሳብ ሳይወጡ ዐሥራው መጻሕፍትን አመስጥረው ስለሚያስረዱ ነው፡፡ ከድርሳነ ኢያቄም ወሐና የምናስተውለውም ይህንኑ ነው፤

የሚል ቅደመ ጥያቄ የተሰጠ መልስ ይነበባል፡፡[4]

ከግእዝ ወደ አማርኛ በመምህር ተስፋ ሚካኤል ታከለ ተተርጒሞ፣ በማኅበረ ቅዱሳን ኤዲቶሪያል ቦርድ «ታርሞና ተስተካክሎ»፣[5] በማኅበሩ አሳታሚነት የታተመው ይህ መጽሐፍ ከመግቢያው ውጪ 128 ገጾች ያሉትና በሦስት ክፍሎች ማለትም፡-

---

[1] ከዚህ በፊት «በግእዝ ቋንቋ በብራና» የነበረውን መጽሐፍ፣ ወደ አማርኛ ቋንቋ በመተርጎም መግቢያውን ሳይጨምር በ128 ገጽ ያደራጁትና በ2007 ዓመተ ምሕረት ለንባብ ያበቁት መምህር ተስፋ ሚካኤል ታከለ እንደ ሆኑ ተገልጿል፡፡ በመጽሐፉ በገጽ 105 ላይ «ጸሐፊው ተስፋ ሚካኤልንም ከማይዳሰስ የርኩሰት ኀጢአታዊ መንገድ ያድነው» ተብሎ የተገለጸው፣ ተርጓሚውን መምህር ተስፋ ሚካኤልን ይሁን ወይም ደግሞ በግእዝ ቋንቋ በብራና ተጽፏል ተብሎ የሚነገረውን ግልጽ አይደለም፡፡

[2] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ገጽ 105፡፡

[3] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) የመግቢያው ሁለተኛው ገጽ አንቀጽ 2፡፡

[4] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) የመግቢያው ሁለተኛው ገጽ አንቀጽ 2፡፡

[5] «ታርሞና ተስተካክሎ» የሚለውን ስመለከት የቅዱሳኑን «እውነተኛ» ታሪክ የያዘው ድርሳን፣ ሳይታረምና ሳይስተካከል ቢወጣ ምን ዓይነት መልክ ይኖረው ነበር? ደግሞስ ‹በፈቃደ

1. ድርሳነ ኢያቄም ወሐና፣
2. ተኣምረ ኢያቄም ወሐና፣ እና
3. መልክአ ሐና ወኢያቄም የተከፈለ ነው፡፡

መጽሐፉ ተስፋ እንደተደረገበት፤ «... <u>በመጽሐፍ ቅዱስ በስውር የሚታወቀውን</u> ...» የቅድስት ማርያም ወላጆችን ማንነት እንድናውቅ ይረዳን ይሆን? የምእመናንን ችግር ለመፍታትስ ምን ያህል ይረዳል? «... <u>ለጸሎት፣ ለትምህርትና ለተግሣጽ</u> ...» የሚረዳና ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ የመጽሐፍ ቅዱስን ምስጢር ለማስረዳት ተቻለው ወይስ...? የሚሉትንና ሌሎች ነገሮችንም በማንሣት መጽሐፉን የመመርመር ሥራ እንሠራለን፡፡ በተለይም መጽሐፉ ቃለ እግዚአብሔር ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከሌሎች የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ጋር ተግባቦት አለውን? የሚለው ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ሁለቱን ሰዎች (ኢያቄምንና ሐናን) በተመለከተ ሐሳብ አስተያየት ማቅረብ ሳይሆን፤ በሁለቱ ሰዎች ስም ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባውን መጽሐፍ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት የራቀ መሆኑን የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንዲመለከቱት መጠቈም ነው፡፡

መጽሐፉን በምዕራፍ ከመከፋፈል ይልቅ በርዕስ እየለዩ ማስቀመጡ የተሻለ ሆኖ ስለ ተገኘ ይህን መንገድ ተከትያለሁ፡፡ ከመጽሐፉ የተወሰዱ ምንባባትን አንባቢው በቀላሉ እንዲለያቸውም ከስራቸው ጎላ ያለ መስመር ተደርጎባቸዋል፡፡

በንባብዎ ሁሉ አንዳች የሚጠቅም ነገር እንዲያገኙ ጸሎቴ ነው!!!

---

እግዚአብሔር፣ በመንፈስ ቅዱስ በመነዳትና «ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ሳይወጡ» የተጻፉ ናቸው፣ ተብሎ ከሚታመንባቸው መጻሕፍት አንዱ ነው የሚባለውን ድርሳን ለማረምና ለማስተካከል የተቀመጠው መስፈርት ምን ይሆን? የሚሉ ጥያቄዎችን ፈጥሮብኛል፡፡

# ጻጋና ጽድቅ በሐና ተሰጠን

የቤተ ክርስቲያን መመሪያ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ጻጋና እውነት በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በሚከተለው መልኩ ያስቀምጣል፤

- «ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ»፡፡[6]
- «ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ»፡፡[7]
- «በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ»፡፡[8]
- «የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ ከእርሱ ነው»፡፡[9]
- «ለእግዚአብሔርም ክብርና ምስጋና ከኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኝ የጽድቅ ፍሬ ሞልቶባችሁ፥ ለክርስቶስ ቀን ተዘጋጅታችሁ ቅኖችና አለ ነውር እንድትሆኑ የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ ዘንድ፥ ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን እጸልያለሁ»፡፡[10]
- «ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን»፡፡[11]

ከዚህ የተለየ ሐሳብ ያላቸው የሚመስሉት የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች[12] ጸጋና ጽድቅ በፍጡር እንደ ተሰጠን አድርገው እንዲህ እያሉ ይሰብኩናል፤

---

[6] ዮሐንስ 1፥17፡፡
[7] 2ኛ ጴጥሮስ 3፥18፡፡
[8] ሮሜ 5፥17 - አጽንዖት የግል፡፡
[9] 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥30-31 - አጽንዖት የግል፡፡
[10] ፊልጵስዩስ 1፥9-11 - አጽንዖት የግል፡፡
[11] 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፥9፡፡
[12] በዚህ መጽሐፍ «የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች» የሚለውን በተደጋጋሚ ያገኛሉ፡፡ በዚህ አገላለጽ የተጠሩት፤ መጽሐፉን በግእዝ ቋንቋ የጻፈው ጸሐፊ፣ ወደ አማርኛ የተረጎሙት መምህር፣ እርማትና ማስተካከያ የሠሩለት አካላትና በማሳተም ለንባብ ያበቁት ናቸው፡፡

<u>የተባረከች ንጽሕት ቅድስት የሆነች ማርያምን ባፈሩልን በሐናና በኢያቄም ጸጋና ጽድቅ ተሰጠን፡፡ በሰማይም ቢሆን በምድርም ቢሆን እንደ እርሷ ያለ አልነበረም፡፡</u>[13]

በዚህ መልእክት ውስጥ ሁለት ስሕተቶች ይታያሉ፤ የመጀመሪያው ጸጋና ጽድቅ በፍጡራን እንደ ተሰጠን መስሎ የቀረበው ነው፡፡ ይህም ደግሞ፤ ጸጋ፣ እውነት፣ ጽድቅ፣ ቅድስናም ቤዛነትም የተደረገልን በመድኅነ ዓለም በክርስቶስ መሆኑን የሚነግረንን ቅዱስ መጽሐፍ አንቀበልም፣ ከዚህ ይልቅ ሸንበቆ በሆኑት በፍጡራን ብንደገፍ ይሻለናል፣ የሚል መልእክት እያስተላለፉ መሆኑን ያሳያል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ፤ «በሰማይም ቢሆን በምድርም ቢሆን እንደ እርሷ ያለ አልነበረም» ያሉት ነው፡፡ እንደ እርሷ ያለ አልነበረም የሚለው (የተነገረው ለማርያም ይሁን ለሐና ብዙም ግልጽ ባይሆንም)፣ የተነገረው ለማንም ይሁን ለማን፣ ‹በሰማይም ሆነ በምድር እንደ እርሱ ያለ የሌለ ሁሉን ቻዩ ፈጣሪ እግዚአብሔር› ብቻ እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ያስተምራል፡፡[14] ነገር ግን ዐሥራው መጻሕፍትን ያስረዳሉ በሚል ሽፋን ከዚህ እውነት ተቃራኒ የሆነ መልእክት ለማስተላለፍ መነሣት፣ ለቅዱሱ መጽሐፍ አልታዘዝም ባይነት ካልሆነ በቀር ምንም ሊባል አይችልም፡፡

## ሕዝቅኤል ያያቸው ዐጽሞች ለሐና የሚመሰክሩ ናቸው

ወገኖቼ ያሉበት የስሕተት ጥግ፣ እነርሱ «ቅዱስ» ነው የሚሉትን ድርሳንን ብቻ ሳይሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስንም በኤዲቶሪያል ቦርድ አርመውና አስተካክለው እስከማውጣት ድረስ የሄደ በመሆኑና፤[15] የፈለጉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ወስደው ከመልእክቱ ውጪ ሲተረጉሙት ሃይ የሚል በመጥፋቱ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ የቤተ ክርስቲያን ልሳን (ጋዜጣ)፣ አልያም የሆነ ዲያቆን እንዲያሳትሙለት ይዞት እንደ መጣው ሐሳብ ወለድ መጽሐፍ ሳያዩት አልቀሩም፡፡

---

[13] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 3 ገጽ 3፡፡

[14] ዘዳግም 15፥11፤ 2ኛ ሳሙኤል 7፥22፤ መዝሙር 70፥19፤ ኤርምያስ 10፥6፤ ሚክያስ 7፥18፡፡

[15] ለአንድ ቤተ እምነት ድጋፍ እንዲሆን በማሰብ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተሠራውን ተገቢ ያልሆነ ሥራ ለመመልከት «ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን» በሚል ርዕስ በ2012 ዓመተ ምሕረት ለንባብ የበቃውን አራተኛውን ዕትም መጽሐፍ ይመልከቱ፡፡

ለዚህም፣ የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች፤

> ሕዝቅኤል የተናገረላቸው ዐሥራ ሁለቱ ደቂቀ እስራኤል ናቸው፡፡ እንደ ደረቁ ዐፅሞች ሁነው በተመለከተ ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ስለ ደረቁ ስለ ዐሥራ ሁለቱ ዐፅሞች ተናገር አለው፣ ስለ እነርሱም ተናገረ፡፡ በእነርሱ ላይም እፍ አለና የሕይወትን መንፈስ ጸጋንም አሳደረባቸው፤ ስለ ተባረከችዋ ሐና እስከሚመሰክሩ ድረስ

በማለት ያሰፈሩት ጥሩ ማሳያ ይሆናል፡፡[16]

በትንቢተ ሕዝቅኤል እንደ ተጻፈው፤ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን አጥንቶች በሞላበት ሸለቆ መካከል አደረገውና በእነዚህ አጥንቶች ላይ ትንቢት ተናገር አለው፤ ሕዝቅኤልም እንደ ታዘዘው ሲያደርግ አጥንቶቹ ተገጣጠሙ፤ ከዚያም ጅማት፣ በመቀጠልም ሥጋ እንደ ገናም ደግሞ ቁርበት ለበሱ፤ በመጨረሻም ትንፋሽ ገብቶባቸው ታላቅ ሠራዊት ሆነው ቆሙ፡፡

የዚህ ሁሉ ክንውን ትርጒም፤ «እነዚህ አጥንቶች የእስራኤል[ን] ቤት ሁሉ...» የሚወክሉ መሆናቸውን ክፍሉ ይናገራል (ቍጥር 11)፡፡ የአጥንቶቹ መድረቅ፤ ተስፋችንም ጠፍቷል፣ ተስፋ ቆርጠናል ማለታቸው ቢሆንም ከመቃብር እንዳወጣቸውና መንፈሱን በውስጣቸው እንደሚያሳድር፣ በሕይወትም እንደሚኖሩ ያበስራቸዋል፡፡[17] የትንቢተ ሕዝቅኤል አንድምታም ይህን ሐሳብ በሚከተለው መልኩ ያቀርበዋል፤ «ታድሰው ሲነሡ ያየሃቸው እሊህ አዕፅማት መላው ቤተ እስራኤል ናቸው፡፡ ዘቤተ እስራኤል ቢል ግን እንደ ሙታን ሥጋችን አለቀ፣ አጥንታችን ደረቀ፣ ተስፋ ሚጠታችን ቀረ ከንቱ ሆነ (ወተገዘርነ) ከአገራችን እንደ ወጣን ከርስታችን እንደ ተነቀልን ቀረነ ከፈጣሪያችን ተለየነ ብለዋልና»፡፡[18] ስለዚህ አጥንቶቹ ለሐና መሰከሩ የሚለው ትረካ በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለ በቤተ ክርስቲያኗ ትርጓሜም የማይታወቅ የስሕተት ትምህርት መሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡

---

[16] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 12 ገጽ 10፡፡

[17] ሕዝቅኤል 37፥1-14 - የ2000 ዕትም ሰማንያ አሐዱ፡፡

[18] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ መጽሐፈ ሕዝቅኤል ከትርጓሜው ጋራ (1916) 367፡፡

# አኗኗሯ ከጥንት የሆነ

ከፍጥረት ወገን ‹መጀመሪያ የሌለውና ከጥንት የነበረ› ተብሎ የሚነገርለት የሌለ ሲሆን፣ ለፈጣሪ ደግሞ አኗኗሩን በተመለከተ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው አይባልለትም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም፣ ጅማሮም ሆነ መጨረሻ የሌለው ዘላለማዊው አምላክ እግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ ደግሞና ደጋግሞ ተናገሯል፡፡ ለአብነትም፤

- «ቤዛ የላቸውምና፥ እግዚአብሔርንም አልፈሩትምና ከጥንት ጀምሮ የነበረ እግዚአብሔር ሰምቶ ያጐሰቊላቸዋል»፡፡[19]
- «እግዚአብሔር ነገሠ፥ ክብርንም ለበሰ፤ እግዚአብሔር ኃይልን ለበሰ፥ ታጠቀም፤ ዓለምን እንዳትናወጥ አጸናት። ዙፋንህ ከጥንት ጀምሮ የተዘጋጀ ነው፥ አንተም ከዘላለም ነህ»፡፡[20]
- «... ከጥንት ጀምሮ እኔ ነኝ ከእጄም የሚያመልጥ የለም፤ እሠራለሁ፥ የሚከለክልስ ማን ነው?»፡፡[21]
- «ይህን የሠራና ያደረገ፣ ትውልድንም ከጥንት የጠራ ማነው? እኔ እግዚአብሔር፣ ፊተኛው በኋለኞችም ዘንድ የምኖር እኔ ነኝ»፡፡[22]

ለማሳያነት የቀረቡት እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ንባባት ላይ እንደ ሰፈረው ከሆነ «አልፋና ኦሜጋ»፣ መጀመሪያውና መጨረሻው፣ ያለውና የነበረው ሊባል የሚገባው ሁሉን ቻዩ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡[23]

የኢያቄም ወሐና መጽሐፍ አዘጋጆች ግን፣ የፈጣሪ የብቻው ገንዘብ የሆነውን ዘላለማዊነት ከእርሱ ነጥቀው ይሁን ወይም ከሌላ ጋር ሊያጋሩት አስበው ግልጽ ባይሆንም፤ «<u>እግዚአብሔርም የቅድስት ሐናን ኀዘን ሰማ፡፡ በዚህች ሌሊትም ቅድስት ሐናን አኗኗሯ ከጥንት በነጭ ወፍ አምሳል የሚያመሰግን ኪሩብ ጋረዷት ከሰማይ ስትወርድ በህልም ተገለጠላት</u>...»[24] የሚል ሐሳብ አስቀምጠዋል፡፡ የተቆረጠ ይኖር?

[19] መዝሙረ ዳዊት 54÷19፡፡
[20] መዝሙረ ዳዊት 92÷2፡፡
[21] ኢሳይያስ 43÷13፡፡
[22]. ኢሳይያስ 41÷4፡፡
[23] ራእይ 22÷13፤ 21÷6፤ 1÷8፡፡
[24] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቊጥር 19 ገጽ 15-16፡፡

ይህ ጽሑፍ ሁለት ስሕተቶች አሉበት፡፡ እነርሱም፤

1. አኗኗሯ ከጥንት የሆነ፡- «ጥንት» የሚለው ትርጉም፣ «ዱሮ ወትሮ ቀድሞ ሥር መሠረት» ማለት ነው፡፡[25] በዚህ ትርጉም መሠረት አኗኗሩ ከጥንት (ከቀድሞ) ጀምሮ የሆነ፣ የሁሉ ነገር ሥር መሠረት የሆነ፣ ሕያው አምላክ እግዚአብሔር ሆኖ እያለ፤ ፍጡርን እንደ ፈጣሪ የሁሉ ነገር ሥር መሠረት እንደ ሆነና አኗኗሩ ከቀድሞ ጀምሮ ነው በማለት የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለፍጡር መስጠት ትልቅ ስሕተት ነው፡፡

2. ኪሩብ ጋረዷት፡- የእግዚአብሔር መላእክት ታላቁን አምላክ እግዚአብሔርን «ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» እያሉ ሌት ተቀን ማመስገን ሥራቸው እንደ ሆነ ቃለ እግዚአብሔር ይናገራል፡፡[26] የድርሳኑ አዘጋጅም በሌላ ስፍራ ላይ ይህን በማጉላት፤ «<u>በሰውና በመላእክት አንደበት በፍጥረታትም ሁሉ አንደበት **ያለዝምታ ያለማቋረጥ** ከምድር እስከ ሰማይ ድረስ ምስጋና ለእርሱ ይገባል ለዘላለሙ አሜን!</u>»[27] ያለውን ረስቶት ይሁን ወይም የሐሳብ ለውጥ አድርጎ ግልጽ ባይሆንም፣ ሁሉን ቻዩን አምላክ አመስጋኝ የሆኑትን መላእክት ፍጡርን የሚጋርዱ አድርጎ አቅርቧል፡፡

# ሔዋን ትሰግድልሻለች

አምልኮ ከምንፈጽምባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ስግደት ነው፡፡ ሰይጣንም ከሚፈልጋቸው ነገሮች ውስጥ ቀዳሚው ስግደት ነው፡፡ እግዚአብሔር ስግደትን በተመለከተ ያለው አቋም ለድርድር የማይቀርብ መሆኑንና ሰይጣንም በልዩ ልዩ ጥበቦች[28] ሰግደትን ለራሱ ለማድረግ ምን ያህል እየተነቀሳቀሰ እንደ ሆነ ስንመለከት በመንፈሳዊው ዓለም ስግደት ምን ያህል ትልቅ ነገር እንደሆነ ለመረዳት አንቸገርም፡፡

---

[25] ባህሩ ዘርጋው ግዛው፣ ዘርጋው ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (መጋቢት 2006) ገጽ 932፡፡

[26] ኢሳይያስ 6፥3፡፡

[27] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 2 ገጽ 2 - አጽንዖት የግል፡፡

[28] በእኛ ቤተ ክርስቲያን የአክብሮት ወይም የጸጋ በማለት ለፍጡራንና ለግዑዛን የሚቀርበውን ስግደት በምሳሌነት መመልከት ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል እግዚአብሔርን ሲያመለክ የነበረው ንጉሥ ሰሎሞን እግዚአብሔርን ያሳዘነው ልቡ ወደ ጣዖት በማዘንበሉ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ተደጋግሞ የሚባል አንድ ነገር አለ፤ ይሄውም እኛ ለቅዱሳን የአክብሮት ስግደት እንሰግዳለን እንጂ አናመልካቸውም የሚለው ነው፡፡ ሰሎሞንን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስነብበው «... ሚስቶቹም ልቡን አዘነበሉት... ሚስቶቹ ሌሎችን አማልክት ይከተል ዘንድ ልቡን አዘነበሉት... ሰሎሞንም የሲዶናውያንን አምላክ አስታሮትን፥ የአሞናውያንንም ርኵሰት ሚልኮምን፥ ተከተለ።... በዚያን ጊዜም ሰሎሞን ለሞዓብ ርኵሰት ለካሞሽ፥ ለአሞንም ልጆች ርኵሰት ለሞሎክ በኢየሩሳሌም ፊት ለፊት ባለው ተራራ ላይ መስገጃ ሠራ፤...»፡፡[29]

በዚህ ክፍል ውስጥ ሰሎሞን መስገጃ መሥራቱንና ሌሎች አማልክትን መከተሉን እንጂ ማምለኩን የሚያሳይ ቃል የለም፡፡ እግዚአብሔር ግን «ሰሎሞንን ተቈጣ»፡፡ ምክንያቱም በልቡ አምልኮት ፈጽሟልና፡፡ ልቡን ከፈቃደ እግዚአብሔር ዘወር አድርጓልና፡፡ «... የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ...» የሚለውን ትእዛዝ በግልጽ ተላልፏልና፡፡

ከዚህም ሌላ ምናሴ፣ ሮብዓም፣ ኤዶምያስ የመስገጃ አጸድ መሥራታቸው ተጽፏል፡፡ የመስገጃ አጸዱ አምልኮ መፈጸሚያ በመሆኑ እግዚአብሔር በጣም አዝኗል፡፡[30] በአንጻሩም እግዚአብሔር ደስ የተሰኘባቸው ነገሥታት ያደረጉትን ስንመለከት ደግሞ ቀዳሚ ሥራቸው የመስገጃ አጸዶችን መሰባበር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡[31]

ሰይጣን ክርስቶስን ሊፈትን በመጣ ጊዜ ካቀረባቸው ሦስት ፈተናዎች መካከል አንዱ «ብትሰገድልኝ» የሚል ነበር፡፡ አንባቢው ልብ እንዲል የሚያስፈልገው «ብታመልከኝ» ወይም «የአምልኮ ስግደት ብትሰግድልኝ» አላለውም፡፡ የሰይጣን ጥያቄ አንዲት ስግደት ነበር፡፡ ኢየሱስም «ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ» የሚልና ቁርጥ ያለ መልስ ነው የሰጠው፡፡ ምንም እንኳን በሰይጣን ንግግር ውስጥ «ስገድልኝ» እንጂ «አምልከኝ» የሚል ቃል ባይኖርም ክርስቶስ ሲመልስለት «እርሱንም ብቻ አምልክ» በማለት ስግደትና አምልኮ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸውን አሳይቷል፡፡

---

[29] 1ኛ ነገሥት 11÷1-10፡፡
[30] 2ኛ ነገሥት 21÷1-3፤ 2ኛ ዜና 11÷5-15፤ 21÷10-11፡፡
[31] 2ኛ ነገሥት 18÷4፤ 23÷8፡ 15፡ 19፤ 2ኛ ዜና 14÷3፡፡

የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች፣ እግዚአብሔር ስግደት ላይ ያለውን ጠንካራ አቋም ያውቃሉ ተብሎ ተስፋ ይደረጋል፡፡ ምክንያቱም የመጽሐፉን አንዳንድ ክፍሎች ስንመለከት አዘጋጆቹ ክርስቲያኖችና የመጽሐፍ ቅዱስ አማኞች ሳይሆኑ አይቀሩም የሚያስብሉ ነገሮች ይታያሉና፡፡ የሚገርመው ግን ሊሰገድለትና ሊመለክ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን እያወቁ እርሱን ለማስቈጣት በሚመስል ሁኔታ ፍጡር ለፍጡር እንዲሰግድ ሲመክሩና ሲያበረታቱ ይታያሉ፡፡ ሐሳባቸውንም ያቀረቡት በሚከተለው መልኩ ነው፤

> ቅድስት ሐና ሆይ፣ ፈጥኖ የሚያልፍ ምድራዊና ኃላፊ ደስታን ተይውና የማያልቀው ዘወትር የማያልፈው ሰማያዊ ደስታ ይገባሻል፡፡ ሔዋን ሠላሳ ወንዶችን፣ ሠላሳ ሴቶችን ወለደች፤ ነገር ግን ምንም አልቀሩም፡፡ ከችግር፣ ከስቃይ፣ ዐፅምን ከመስበር በስተቀር ምንም ያገኘችው የለም፡፡ እርሷም ያንቺን መምጣት ትጠባበቃለች፡፡ በልጅሽ ልጅ /በክርስቶስ/ ትንሣኤን ስታገኝ ትሰግድልሻለች፡፡ ጽኑ የሆንሽ ቅድስት ሐና ሆይ ከአንቺ በፊትም ከአንቺ በኋላም ከነበሩ ሴቶች ይልቅ ምስጋናሽ ምን ይበዛ? እንደ አንቺ ሞገስን አላገኙምና፡፡[32]

ይህ ሁሉ እግዚአብሔርን ለማስቈጣት ሰይጣን የነደፈው እቅድ እንጂ ከእግዚአብሔር ሌላ ስግደት የሚገባው አካል እንደሌለ መጽሐፍ ቅዱስ «በላይ በሰማይ[33] ካለው፣ በታችም በምድር[34] ካለው፣ ከምድርም በታች በውሃ[35] ካለው ነገር

---

[32] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 23 ገጽ 19 - አጽንዖት የግል፡፡

[33] በሰማይ፤ ቅዱሳን መላእክት፣ ሰማይ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት፣ አእዋፋት ይገኛሉ፡፡ መጽሐፉ «በላይ በሰማይ ካለው… የማናቸውንም ምሳሌ… ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም» ሲል እነዚህን ሁሉ ይመለከታል፡፡

[34] በምድር፤ የሰው ልጆች፣ በተለያየ ቅርጽ (መልከአ ምድር) የሚታይ መሬት፣ ልዩ ልዩ እንስሳት፣ ልዩ ልዩ እጽዋት… ይገኛሉ፡፡ መጽሐፉ «በታች በምድር ካለው… የማናቸውንም ምሳሌ… ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም» ሲል እነዚህን ሁሉ ይመለከታል፡፡

[35] በውሃ፤ ራሱን ውሃውን ጨምሮ ልዩ ልዩ እጽዋት፣ የተለያየ ዝርያ ያላቸው ዓሣዎች… ይገኛሉ፡፡ መጽሐፉ «በታች በውሃ ካለው… የማናቸውንም ምሳሌ… ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም» ሲል እነዚህን ሁሉ ይመለከታል፡፡

የማናቸውንም[36] ምሳሌ፣[37] የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም፤[38] በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኀጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወድዱኝ፥ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ

[36] በዚህ ስፍራ ላይ የተገለጡት ሁሉ በባሕርያቸው የሚመለኩ (ጣዖታት የሆኑ) አይደሉም፡፡ ሰዎች ግን በራሳቸው ተነሣሽነት ያለ ባሕርያቸው ስላስቀመጧቸው «አማልክት» ወይም ጣዖታት ይሆናሉ፡፡ በእኛ ቤተ ክርስቲያንም ‹እኛ ቅዱሳንን አናመልክም› የሚል አባባል የተለመደ ነው፡፡ ምንም እንኳ የምናቀርብላቸው የጸጋ ስግደት ነው የሚል ነገር ተደጋግሞ ቢነገርም «የጸጋ» በሚል ስም የተሰጠውም ስግደት የሚገባቸው ባለመሆኑ ያለባሕርያቸው እንዲቀመጡ አድርጓቸዋል፡፡ ስለዚህ «አናመልካቸውም» ቢባልም እየቀረበላቸው ያለው ግን አምልኮት ነው፡፡ የሚያሳዝነው በቅዱሳን ስም እየቀረበ ያለውን ይህን አምልኮት የሚቀበለው ጠላት መሆኑ ነው፡፡

[37] «የማናቸውንም ምሳሌ» የሚለውን በ2000 ዓመተ ምሕረት የታተመው ሰማንያ አሐዱ «የማናቸውንም ምስል» በሚል አስቀምጦታል፡፡ ምሳሌም ሆነ ምስል አንድን አካል እንዲወክል ተደርጎ የሚቀርብ የሰው የእጅ ሥራ ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው በሰማይ ካሉት መላእክትም ቢሆን ወይም በምድር ካሉት ሰዎች መካከል የማናቸውንም ምሳሌ (በስእልም ሆነ በቅርጽ) እንድንሠራ ፈቃድ የለንም፡፡ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ስያሜና ሽፋን ብንሰጠውም እያደረግን ያለነው ነገር እግዚአብሔር አምላክ «ለአንተ አታድርግ» ያለውን ግልጽ ትእዛዝ ለመታዘዝ ፈቃደኛ አለመሆናችንን ያሳያል፡፡

[38] «ለአንተ አታድርግ፣ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም» የሚለው ትእዛዝ ስለ አንድ ነገር ስለ አምልኮት እየተናገረ ቢሆንም ሦስት ደረጃዎችን ግን ያሳየናል፡፡ በመጀመሪያ የራስ ስለማድረግ የሚናገረው ነው፡፡ ይሄውም መልክ በመስጠት (በቀደመው ዘመን በስዕል ወይም በምስል፣ በዘመናችን ደግሞ በተንቀሳቃሽ ስልካችን ወይም በሰውነታችን በንቅሳት) መያዝን ወይም ወደ ቤታችን ማስገባትን ያሳያል፡፡ ቀጣዩ ደግሞ የራሴ ያደረኩትን ያንን ባዕድ ነገር ከፊቴ አስቀምጬ የማቅርብለትን ስግደት ያሳያል፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች ስግደትን በሁለት በመክፈል አንደኛው የአምልኮት ስግደት የሚባል እንደ ሆነ ሲናገሩ ይሰማል፡፡ በዚህ ስፍራ ላይ ስግደቱ ራሱን ችሎ የቆመ መሆኑን ስንመለከት ስግደት አንዲት እርሷም አምልኮ የሚፈጸምባት መሆኗን መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህም ሰይጣን ጌታችንን ሲፈትን ያቀረበውን ጥያቄና መልስ ለምሳሌነት ማቅረብ ይቻላል፤ ሰይጣን ለኢየሱስ የዓለምን መንግሥታት እንደሚሰጠው ቃል የገባው «ወድቀህ ብትሰግደልኝ» በማለት ብቻ ነው እንጂ «የአምልኮ ስግደት» የሚል የለውም፡፡ የሰይጣን ጥያቄ ለአንዳንዶች ግልጽ ያልሆነ ቢመስልም ኢየሱስና እርሱ ግን ተግባብተዋልና ኢየሱስ «ሂድ፣ አንተ ሰይጣን፤ ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአልና አለው» (ማቴዎስ 4÷8-10)፡፡ የክርስቶስ መልስ «ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ» የሚል መሆኑን ልብ ይበሉ፡፡ ስግደት ሁለት ዓይነት ትርጒም ያለው እኛ ጋር ብቻ ነው፡፡ ሰይጣን ለኢየሱስ ስግደት ብቻ ጠየቀው፣ ኢየሱስ ደግሞ ስግደት ውስጥ አምልኮ መኖሩን ሊያሳየን የሚችል መልስ ሰጠው፡፡ በመጨረሻ የተቀመጠው አታምልካቸው የሚለው ነው፡፡ በዚህም ስግደትና አምልኮት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡ አምልኮ በተለያዩ መንገዶች (በዝማሬ፣ በጸሎት፣ በመታዘዝ፣ በስግደት…) የሚፈጸም ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ስግደት ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትም፤ «ሰው በአምላኩ ፊት አምልኮትን…» የሚፈጽምበት መሆኑን አስፍሯል (የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (ዐዲስ አበባ፣ 1998 - ስምንተኛ ዕትም) ገጽ 84)፡፡ በዚህ ትእዛዝ በመጀመሪያ የራስ በማድረግ፣ ከዚያም በመስገድ አምልኮ መፈጸም የሚገባ አለመሆኑን አሳይቶናል፡፡

እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና» በማለት ዘግቶታል፡፡[39]

ሌላው ደግሞ፤ «ያንቺን መምጣት ትጠብቃለች» የሚለውም ከእውነታው የራቀ አስተሳሰብ ነው፡፡ አዳምና ሔዋን በበደሉ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ የሰጣቸው የተስፋ ቃል ውስጥ፤ «በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ» በሚል ሊጠብቁት የሚገባቸው ማንን እንደ ሆነ አመላክቷቸዋል (ዘፍጥረት 3÷15)፡፡ በቀደመው ኪዳን የነበሩ ነቢያት ሁሉ ሲናገሩ የነበሩት፣ በጌታችን ዘመነ ሥጋዌ የነበሩ ሰዎችም በተስፋ እየጠበቁት የነበረው መሲሑን መሆኑን ቅዱሱ መጽሐፍ ያስረዳል፡፡

ከዚህም ሌላ፤ «በልጅሽ ልጅ /በክርስቶስ/ ትንሣኤን ስታገኝ ትሰግድልሻለች» በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ፤ ትንሣኤን የሚሰጠውና ስግደት የሚቀበለው አካል የተለያዩ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሚገባውን ለሚገባው ያለ መስጠት ችግር ነው፡፡ እንዲህ ያለው ችግር በሁሉም አዋልድ መጻሕፍት ውስጥ የሚታይ ነው፡፡

## ጥቅስ ማጣመም

የመጽሐፉ አዘጋጆች የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የጎደላቸውና ከዚህም የተነሣ ጥፋት የሚያጠፉ ሰዎች አይደሉም፡፡ ከዚህ ይልቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀታቸው ጥሩ የሚባል ሆኖ እያለ እውቀታቸውን ግን ለገዛ ጥፋታቸው ጥቅሶችን በማጣመም ያለመልእክታቸው እንዲናገሩ የሚያደርጉ ሰዎች ናቸው፡፡

ለዚህም ጥሩ ማሳያ የሚሆነው «<u>ነቢያት ‹በብዙ ድካምና መከራ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንገባ ዘንድ አለን›</u> » ብለዋል በሚል የሰፈረው ነው፡፡[40] በዚህም ክፍል ሁለት መሠረታዊ ችግሮች ይታያሉ፤

1. «ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል» ያሉት የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንጂ ቀደም ሲል የነበሩ ነቢያት አይደሉም፡፡[41]

---

[39] ዘጸአት 20÷4-6፡፡

[40] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 26 ገጽ 21-22፡፡

ሐዋርያት የተናገሩትን ነቢያት ነው የተናገሩት የተባለበት ምክንያት በመጽሐፉ ላይ በሰፈረው ታሪክ መሠረት ሐዋርያትን መከተት ለመጽሐፉ አዘጋጆች የሚያስቸግር በመሆኑ ነው፡፡

2. የመጽሐፉ ስሐተት የጥቅሱን ባለቤት መለወጥ ብቻ ሳይሆን ያለ ዐወዱ በማስፈሩም ነው፡፡ ሐዋርያት እንዲህ ያሉት ወደ ሊቃኦንያ ከተማዎች ገብተው ሲሰብኩና ተኣምራት ሲያደርጉ ሕዝቡ አማልክት ናቸው ብለው ሊሰዉላቸው ደፋ ቀና ማለት በመጀመራቸው ነው፡፡

ጳወሎስና በርናባስም ልብሳቸውን ቀደው በመጮህ በጭንቅ ካስቆሟቸው በኋላ «አይሁድ ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን መጡ፤ ሕዝቡንም አባብለው ጳውሎስን ወገሩ የሞተም መስሎአቸው ከከተማ ወደ ውጭ ጐተቱት»፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ ጳውሎስ ተነሥቶ ወደ ደርቤን ገብተው «የደቀ መዛሙርትን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና፡- ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ፣ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም ወደ አንጾኪያም ተመለሱ»፡፡[42]

ታዲያ የመጽሐፉ አዘጋጆች የሠሩት ስሐተት ምንድን ነው? ከተባለ በመጽሐፋቸው ውስጥ ያሰፈሩት ታሪክ፤ «ሐናንም በመጀመሪያ ልጅን በማሳጣት ምግብን በመንሣት ፈተናት፡፡ የሕሊናዋን ትዕግስት አውቆ በእስራኤል ወገኖች ሁሉ ዘንድ ግፍን ትቀበል ዘንድ በብዙ ኀዘን ስቃይም በጎ ትርፍንና መልካም ዕድልን ሰጣት፤ የሚነጥቃትም የለም፡፡ ነቢያት ‹በብዙ ድካምና መከራ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንገባ ዘንድ አለን› እንዳሉ» የሚልና ከተነገረበት መሠረተ ሐሳብ የተለየ መሆኑ ነው፡፡

አንባቢው አሁን በራሱ መመልከት እንደሚችለው የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ይህን ማለታቸው የእግዚአብሔርን ቃለ በማስተማራቸው ስለ ደረሰባቸው መከራ ሲሆን ይህ ቃል ለሐና የተነገረላት ግን ልጅና ምግብ በማጣቷ ስለ ደረሰባት ችግር ነው፡፡ ስለዚህ በሁለቱ መጻሕፍት መካከል የታሪክም የእውነታም ልዩነት መኖሩ ግልጽ ስለሆነ ከዚህ በላይ ማለቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡

---

[41] የሐዋርያት ሥራ 14÷21-22፡፡

[42] የሐዋርያት ሥራ 14÷1-22፡፡

# ሕይወታችን ማርያም ናት

መጽሐፍ ቅዱስ «የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት፤ እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፥ ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን» በማለት «የሕይወት ራስ» ክርስቶስ መሆኑን ሲናገር፤[43] «ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን» በማለት በሕይወት ለመኖር የሚቻለው በእርሱ እንደ ሆነ ያስተምራል፡፡[44]

እንደገናም ደግሞ ኋለኛው አዳም ተብሎ የተጠራው መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ ሕይወትን የሚሰጥ መሆኑን፤[45] ይህን ሕይወት ሊሰጠንም ራሱን አሳልፎ በመስጠት ስለ እኛ መሞቱን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡[46] ለዚህም ነው ሐዋርያው ዮሐንስ «ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም» ያለው፤ «እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው[ና]»፡፡[47]

የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ቅዱሱ መጽሐፍ ከዚህም በላይ በብዙ መንገድና ሁኔታ የሰው ሁሉ ሕይወት ክርስቶስ እንደ ሆነ ቢያስገነዝበም፣ እንዲህ ያለውን እውነት መቀበል የከበዳቸው የመጽሐፉ አዘጋጆች፤ «<u>ቅድስት ሐና ሆይ ብፅዕት ሣራና ርብቃ ከእግሮችሽ የአንዲቷ ጥፍር ዋጋ አይሆኑም፡፡ የሕይወት እናት ነሽና ሕይወታችንም እመቤታችን ናት</u>» በማለት እንግዳ ትምህርት አስተላልፈዋል፡፡[48] በዚህም ሐሳባቸው ልዩ ልዩ ስሕተቶችን አቅርበዋል፤

- ሣራና ርብቃ ታሪካቸው በብሉይ ኪዳን የሰፈረ፣ ከሐናም ሆነ ከማርያም ቀደም ብለው የነበሩ ታላላቅ ሴቶች ናቸው፡፡ ሣራ የአብርሃም ሚስት ስትሆን የተስፋ ልጅ የሆነውን ይስሐቅን በእርጅና ዘመኗ በመሳም ሳቅ በሳቅ የሆነች ሴት ናት፡፡ ርብቃ ደግሞ «የአብርሃም ወንድም፥ የናኮር የልጅ ልጅ፥ የላባ እኅት… የይስሐቅ

---

[43] የሐዋርያት ሥራ 3፥15፡፡
[44] ሮሜ 6፥7-8፡፡
[45] 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥45፡፡
[46] 1ኛ ተሰሎንቄ 5፥10፡፡
[47] 1ኛ ዮሐንስ 5፥12፣ 20፡፡
[48] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 25 ገጽ 20፡፡

ሚስት...» የያዕቆብና የኤሳው እናት ናት፡፡[49] የሥላሴ ፍጡር የሆኑትና እግዚአብሔር ታላላቅ ነገር የሠራባቸውን እነዚህን እናቶች፣ የሐና የእግሮቿ የአንዷቷ ጥፍር እንኳ ያህል ዋጋ የሌላቸው መሆናቸውን ያሰፈረው ጸሐፊ፣ ይህን ለማለት ምንም ያቀረበው ምክንያት ባይኖርም፣ ተቈርጦ የሚጣለን ጥፍር ከቅዱሳን እንስቶች ጋር ለማወዳደርና ብሎም ጥፍሩን አልቆ ቅዱሳኑን ለማሳነስ መጀገኑ የሚገርም ነው፡፡[50]

- ሐናን «የሕይወት እናት ነሽ» ልጇን ደግሞ «ሕይወታችን» በማለት ማርያም ለሁሉ ሕይወት እንደ ሆነች አስመስሎ አቅርቧል፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል እንደ ተባለው ሕይወት የሆነውን ክርስቶስን በመጋረድ ዓይናችንን ፍጡር ላይ እንድናደርግ የተሠራ ሥራ ነው፡፡

በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ እንደተባለው ክርስቶስ ሕይወት መሆኑን በመጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ የሰፈረ ሲሆን ከክርስቶስ ውጪ ሕይወት የሆነ ፍጡር እንዳለ የተጻፈ ነገር ለማግኘት አይቻልም፡፡ ለዚህ ደግሞ ራሱ ክርስቶስ የተናገረውን ማስፈሩ የተሻለ ነው፡፡ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም»፡፡[51] በዚህ በክርስቶስ ንግግር ውስጥ «እኛ» ሳይሆን «እኔ» ማለቱን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሕይወት የሆነን አንድ ብቻ እርሱም ክርስቶስ መሆኑን ያሳያል፡፡

## ማርያም መባል በለምጽ ያስመታል!

በመጽሐፍ ቅዱስ ከኢየሱስ እናት ከቅድስት ማርያም ሌላም «ማርያም» በሚል ስም የተጠሩ ሰባት ሴቶች መኖራቸው ይታመናል፡፡ እነርሱም፤

[49] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1998 - ስምንተኛ ዕትም) ገጽ 68፡፡

[50] ምናልባት በአካላዊ ቁመና ሐና ከእነርሱ ይልቅ ትልቅ መሆኗን ለማሳየት ፈልጎ ነው እንዳይባል እነርሱ ከእርሷ የአንዲት ጣት ጥፍር ያነሱ ከሆኑ፣ እርሷ ምን ያህል ግዙፍ ብትሆን ነው? የሚል ጥያቄ ማጫሩ አይቀርም፡፡ ይህን ሐሳብ ሳነብ «... ዓይኑ በመላእክት ክንድ ዘጠኝ ክንፉ ሰማንያ ወርዱ መቶ አርባ ቁመቱ በመላእክት ክንድ ስምንት ሺ የሚሆን ብርያል የተባለው ዲያብሎስ ይመጣል፡፡... በመላእክት ክንድ ሰባት የሚሆን ጥርሱን ይሰብራል፡፡... የእጁ ጥፍር መቶ ዓርባ ክንድ ይሆናል» በሚል ስለ ሰይጣን የተጻፈውን አስታወስኩ (ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ ድርሳነ ሰንበት - ግእዝና አማርኛ (1987) ገጽ 12 እና 89፡፡)፡፡

[51] ዮሐንስ 14፥6፡፡

1. የሙሴ እኅት፣[52]
2. የዬቶር ልጅ፣[53]
3. የማርታና የአልዓዛር እኅት፣[54]
4. መግደላዊት ማርያም፣[55]
5. የታናሹ ያዕቆብና የዮሳም እናት፣[56]
6. የቀለዮጳ ሚስት፣[57]
7. የማርቆስ እናት[58] ናቸው፡፡[59]

እነዚህ ሴቶች የየራሳቸው የተለያየ ታሪክ አላቸው፡፡ ከዚህም ውስጥ የሙሴ እኅት ማርያም በለምጽ ተመትታ እንደ ነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል፡፡ የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች ማርያም በለምጽ ስለተመታችበት ምክንያት ያሰፈሩት የተለየ ትምህርት የሚከተለውን ይመስላል፤

> የልጃቸውን ስም ሲያወጡም ዮካቤድ እንደ በመጀመሪያ ልጅ ሳያገባት ልጇን ማርያም አለቻት፤ ስለዚህ ታመመች፤ በለምጽ ተያዘች፡፡ ከለምጿ እስከምትፈወስ ድረስ በበሽታው ምክንያት ከከተማው ወደ ውጪ ወጣች፡፡ **አሪትም ‹ሙሴን ባማችው ጊዜ በለምጽ ተያዘች› ይላል፡፡ እኔ ግን** እግዚአብሔር ስለ እናቱ በመቅናቱ ሊያጠፋት በወደደ ጊዜ ምክንያትን ፈለገላት **እላለሁ**፡፡ እርሷ በእናቱ ስም ትጠራ ዘንድ አልፈቀደምና፡፡[60]

---

[52] ዘጸአት 15÷20፡፡
[53] 1ኛ ዜና መዋዕል 4÷17፡፡
[54] ዮሐንስ 11÷1፡፡
[55] ዮሐንስ 20÷1-18፡፡
[56] ማርቆስ 15÷40፡47፡፡
[57] ዮሐንስ 19÷25፡፡
[58] የሐዋርያት ሥራ 12÷12፡፡
[59] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (1998 - ስምንተኛ ዕትም) ገጽ ገጽ 51-52፡፡
[60] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 27 ገጽ 22 አጽንዖት የግል፡፡

ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እንደተባለው የመጽሐፉ አዘጋጆች የሠሩትን ስሕተት ሁሉ የሠሩት የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ስለማያውቁ ሳይሆን እያወቁ ሆነ ብለው (በድፍረት) ነው፤ ቀደም ሲል የቀረበው መልእክታቸው ይህን በሚገባ ያሳያል፡፡ በተለይ በዚህ ክፍል የሰዎቹን የልብ ጥንካሬና ሆነ ብለው የማጥፋት ተግባራቸው «አሪትም... ይላል፡፡ እኔ ግን... እላለሁ» በሚል አስቀምጠውታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የሙሴ እኅት በለምጽ የተመታችበትን ምክንያት ከአሮን ጋር ስለ ሙሴ ክፉ ነገር በመነጋገራቸው መሆኑን በሚገባ ያሰፈረ ቢሆንም፤[61] የድርሳነ ኢያቄም ወሐና ጸሐፊዎች ግን ይህን አንቀበልም የሚል ግልጽ ተቃውሞ በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡

ይህን ለማድረግ የፈለጉትም «ማርያም» በሚለው ስም ከኢየሱስ እናት ከቅድስት ማርያም ውጪ ማንም ሊጠራበት አይችልም በሚል እሳቤ መሆኑን «በእናቱ ስም ትጠራ ዘንድ አልፈቀደምና» በማለት ገልጸውታል፡፡

ቀደም ሲል እንደቀረበው የተለያዩ ሴቶች በዚህ ስም የተጠሩ ቢሆንም በዚህ ምክንያት ቅጣት የተቀጡ መሆናቸው ግን አልተጻፈም፡፡ ከዚህ ይልቅ ራሱ ጌታችን መግደላዊት ማርያምን «ማርያም» ብሎ በመጥራት ከዚህ ስም ጋር በተያያዘ ሌሎች ቢጠሩበት ምንም ችግር የሌለ መሆኑን አሳይቷል ፡፡[62]

ከሰባቱ ሴቶች አንዷቱን ብቻ በለምጽ ቀጥቷታልና ይህን ስም መጠቀም ለቅጣት ይዳርጋል የሚለው የመናፍቃኑ የተሳሳተ መልእክት ቀሪዎቹ ስድስቱ ለምን ሳይቀጡ ቀሩ? ሊያውም የሚበዙቱ በእናቱ ስም እየተጠሩ ጌታችንን ሲያገለግሉ የደቀ መዛሙርቱን ስም ሲቀይር የእነርሱን ዝም ያለበት ምክንያት ምን ይሆን? ያስብላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሙሴ እኅት ማርያም፣ «ማርያም» ተብላ የተጠራችው ገና ድንግል ማርያም ባልተወለደችበት ዘመን መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ እውነቱ ይህ ከሆነ የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች ድንግል ማርያም ገና ሳትወለድ እግዚአብሔር በእናቱ ስም ሌላ ሴት ልትጠራ ስላልፈለገ የሙሴን እኅት ማርያምን በለምጽ መታት እያሉ መተረክ ለምን አስፈለጋቸው?

ለዚህ ሐሳብ ማጠናከሪያ እንዲሆን «<u>ለእስራኤል ልጆች በተናገራቸው ጊዜ ስለ ስም ቅንአት ሙሴ የተናገረውን ሰሙት፡፡ እግዚአብሔር ከመካከላችሁ እንደ እኔ ያለ</u>

---

[61] ዘኁልቍ 12፥1-16፡፡
[62] ዮሐንስ 20፥16፡፡

ነቢይን ያስነሣላችኋል፤ ስሙም እግዚአብሔር ይባላል፡፡ የዚህን ነቢይ ትእዛዝ የማይቀበልም ይህቺ ነፍስ ከሕዝቧ ተለይታ ትጥፋ አለ» በሚል የሰፈረው አብሮ መታየት ይኖርበታል፡፡[63]

ሙሴ ያለው ምን ይሆን? አንባቢው በራሱ አንብቦ ያስተውል ዘንድ የሙሴን ንግግር ከዚህ በታች እንዲሰፍር ተደርጓል፤

> አምላክህን እግዚአብሔርን በኮሬብ ስብሰባ ተደርጎ በነበረበት ቀን፡- እንዳልሞት የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ደግሞ አልስማ፣ ይህችን ታላቅ እሳት ደግሞ አልይ ብለህ እንደ ለመንኸው ሁሉ፣ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፣ እርሱንም ታደምጣለህ፡፡ እግዚአብሔርም አለኝ፡- የተናገሩት መልካም ነው፤ ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፣ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ፡፡[64]

የመጽሐፉ አዘጋጆች «ስሙም እግዚአብሔር ይባላል» የሚለውን ከየት እንዳገኙት ግልጽ አላደረጉም፡፡ ይህን ቃል ለመጨመር የፈለጉበት ምክንያት ግን ቀደም ሲል እንደ ተባለው የማርያምን ስም ለሌላ ሰው መስጠት ያስቀጣል በሚል ላቀረቡት መልእክታቸው ማጠናከሪያ እንዲሆናቸው ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከላይ ባሉት ሁለት አናቅጽ እንደታየው ድንግል ማርያምን የእግዚአብሔር እናት እያሉ መጥራት በምሥጢረ ሥላሴ አስተምህሮ ላይ የስም ተፋልሶ የሚፈጥር ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚለው ስም የሦስቱ አካላት የአንድነት ስም እንደ ሆነ በምታምን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ወልድን በሥጋ ወለደችው ማለት እየተቻለ በአንድነት ስማቸው የእግዚአብሔር

---

63 ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 28 ገጽ 23፡፡

64 ዘዳግም 18፥15-19፡፡

እናት እያሉ መጥራት ሥላሴን ወልዳለች የሚል ስሕተት ሊያስከትል እንደሚችል ማስተዋልም ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አንዲት ግብፃዊት ለልጇ እግዚአብሔር የሚል ስም ሰጥታ እስራኤላውያን የግብፃዊቷን ልጅ ወደ ሙሴ አምጥተው በችሎት ፊት እንዳቀረቡት የተጻፈ ትረካ አለ፡፡ በችሎቱ ፊትም የእግዚአብሔርን ስም በመጠቀሙ እግዚአብሔር ውሳኔ ስለ ሰጠ ልጁ በድንጋይ ተወግሮ ክፉ አሟሟት መሞቱ ተጽፏል፡፡ ከዚህም በኋላ «እኔም እንዲህ እላለሁ ድንግልና ብሩክ የሆነች የአምላካችን የአማኑኤልን እናት የሐናና የኢያቄምን ልጅ ስም ያረከሰ ሁሉ ሞትን ይሙት በነፍሱም በሥጋውም ጤናን አያገኝ ለዘላለሙ አሜን» የሚል እርግማኑን ያስቀምጣል፡፡[65] ይህም ቢሆን ያው እንደ ተለመደው ድንግል ማርያምን ከሰው የተለየች አድርጎ ለማሳየትና ሰው በፍርሐት እርሷን እንዲያከብር ለማድረግ የተሠራ ሥራ ነው፡፡

## በእንቁላሉ ያልተቀጣው...

ልጁ እንቁላል ሰርቆ ሲያመጣላት ሳትቀጣው የቀረችው እናት፣ የስርቆት ሥራውን አሳድጎት በሬ ላይ ሲደርስ ተይዞ አይታ ብታለቅስ፤ «አይ እናቴ! ምነው በእንቁላሉ ጊዜ በቀጣሽኝ!?» አለ እንደ ተባለው የዚህ መጽሐፍ አዘጋጆችም መጽሐፍ ቅዱስን ገና መዳፈር እንደ ጀመሩ «ተዉ» ብሎ የሚቈጣና የሚቀጣ አላገኙምና ጥፋታቸው በመጠንም በደረጃም እየጨመረ መጥቷል፡፡ እንዲህ የተባለው ያለ ምክንያት አለመሆኑን ለመረዳት ቀጣዩን ምንባብ ይመልከቱ፡፡

«ነቢዩ ምስክር እንደ ሆነው አናጢዎች የናቋት ይህቺ ድንጋይ [ሐና] የቤት ማዕዘን ማቅኛ ሆነች»፡፡[66] መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ የሌለው ሰው ምናልባት «ታዲያ እንዲህ መባሉ ምን ችግር አለው?» ብሎ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የሕይወታቸው መመሪያ ያደረጉ ሰዎች ግን ቀደም ሲል በብሉይ ኪዳን «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፥ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ» መባሉንና በኋላም በዐዲስ ኪዳን «ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፦ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፤ ይህም ከጌታ

[65] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 30 ገጽ 24-25፡፡

[66] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሠሉስ ቍጥር 16 ገጽ 37 - አጽንዖት የግል፡፡

ዘንድ ሆነ፥ ለዓይኖቻችንም ድንቅ ነው የሚለውን ከቶ በመጽሐፍ አላነበባችሁምን?» በማለት ጌታችን መናገሩን ያስታውሳሉና ይህ ጥቅስ ለፍጡር ተገቢ አለመሆኑን ይረዳሉ፡፡[67]

ሐዋርያው ጴጥሮስም የክርስቶስን ትምህርት በማጠናከር የሚከተለውን ተናግሯል፤

> እናንተ በሰቀላችሁት እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደህና ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ፥ ለእናንተ ለሁላችሁ ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን፡፡ እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፥ የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው፡፡ መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና፡፡[68]

ከዚህ ክፍልም በግልጽ እንደሚታየው፣ አስገራሚውና አሳዛኙ ነገር፣ የድርሳኑ አዘጋጆች ያለ ገደብ መሠረታዊ ዶግማ እስከ ማፍረስ የደረሰ ኑፋቄ እያዘጋጁ ሲያሰራጩ ሃይ ባይ አለመኖሩና ምእመኑን የማስጠንቀቅ ሥራ አለመሠራቱ ነው፡፡

## …ወደ በሬ አሳደገው

በእርግጥም ሰዎቹ በእንቁላሉ አልተቀጡምና ጥፋታቸውን «ወደ በሬ» እንዲህ በሚል አሳድገውት ይገኛሉ፡፡ «…<u>እርሷም [ማርያም] በምድርና በሰማይ **አስታራቂ ሆነች**፣ በእርሷም **ዓለም ሁሉ ተስማማ (ዳነ)**፣ **ጥላቻን ገደለች**፣ የጠላትም **ግድግዳ ተናደ**፣ ለራቁትም **ሰላምን አደረገች**፣ ለቀረቧትም **ደኅንነትን አደረገች**</u>»፡፡[69]

---

[67] መዝሙረ ዳዊት 117፥22፤ ማቴዎስ 21፥42፤ ማርቆስ 12፥10-11፤ ሉቃስ 20፥17፡፡
[68] የሐዋርያት ሥራ 4፥10-12::
[69] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሠሉስ ቍጥር 16 ገጽ 37-38 - አጽንዖት የግል፡፡

ስሕተታቸውን ደረጃ በደረጃ እያሳደጉት የመጡት ጸሐፊዎች አንባቢዎቻቸውን ከክርስቶስ ለመለያየት ያላቸውን ቁርጠኛ አቋም በዚህ መልእክታቸው ጠንከር አድርገው በገሐድ አሳይተዋል፡፡

የመጀመሪያው ስሕተታቸው ፍጡርን የምድርና የሰማይ አስታራቂ አድርገው በማቅረብ፣ «እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፣ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ሥራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በሥጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ» ተብሎ የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል ፊት ለፊት መቃወማቸው ነው፡፡[70] እንግዲህ ሐዋርያው «በሞቱ በኩል» መታረቃችንን እንዲህ በግልጽ እያስተማረ እነርሱ ግን ሞቱን በሚያናንቅ መልኩ ሌላ አስታራቂ ያለ በማስመሰል መጻፋቸው ትልቅ ድፍረት ነው፡፡

ሁለተኛው ስሕተታቸው፤ ዓለም ሁሉ የዳነው «በእርሷ» ነው በሚል ብቸኛውን አዳኝ ለማስተው የሠሩት ሥራ ነው፡፡ ይህም ሐዋርያው «… ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር…» ነው እያለ ያስተማረውን ትምህርት የሚቃወም ነው፡፡[71] ስለዚህ ዓለም ሁሉ የዳነው በክርስቶስ መሆኑን የሚነግሩንን ቅዱሳት መጻሕፍት ትተን ሌላ እንግዳ ትምህርት እንቀበል ዘንድ ተገቢ አይደለም፡፡[72]

ሦስተኛው ስሕተታቸው፤ «ጥላቻን ገደለችው» በሚለው ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህም «ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው» በሚል የሰፈረውን ቅዱስ ቃል በገሐድ አንቀበልም ማለታቸውን ያሳያል፡፡[73]

አራተኛው ስሕተታቸው፤ «የጠላትም ግድግዳ» የተናደው በማርያም ነው በማለት ያስቀመጡት ነው፡፡ ይህንም ያደረጉት እንደ ተለመደው «እርሱ ሰላማችን ነውና፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን ዐዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር

[70] ቈላስይስ 1፥21-22 - አጽንዖት የግል፡፡
[71] 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥9፡፡
[72] ዮሐንስ 3፥16-17፡፡
[73] ኤፌሶን 2፥16፡፡

ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ» በሚል የተቀመጠውን የእግዚአብሔር ቃል በመቃረን ነው፡፡ ይህንም ያደረጉት ስለማያውቁት ነው ለማለት ይከብዳል፡፡[74]

አምስተኛው ስሕተታቸው፤ ርቀው ለነበሩት ሰላምን ያወጀችው እርሷ እንደ ሆነች በማስመሰል «አደረገች» ሲሉን ቅዱሱ መጽሐፍ ግን ይህ ሰላም የተገኘው በጌታችን መሆኑን «መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን፣ ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምስራች ብሎ ሰበከ» እያለ ያስነብባል፡፡[75]

ስድስተኛው ስሕተታቸው፤ «ለቀረቧትም ደኅንነትን አደረገች» በሚል የቀረበው ነው፡፡ በዚህ መልእክታቸው ውስጥ ድኅነት የተገኘው «በእርሱ» ሳይሆን «በእርሷ» ነው ማለታቸውን ማስተዋል ይገባል፡፡ ይህም ታዲያ «አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል» በሚል ከቀረበው ከሐዋርያው ትምህርት የተለየና እንግዳ ትምህርት በመሆኑ ሐዋርያው እንዳለው የተረገመ ነው፡፡[76]

## የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ

ወደ አንድ ቤት ለመግባትም ሆነ ወዳጅ ዘመድን ለማስገባት የበሩ ቁልፍ የሚኖራቸው የቤቱ ባለቤቶች ብቻ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ ምናልባት የቤቱ ባለቤቶች ለአጭርም ሆነ ረዘም ላለ ጊዜ ወደ ሌላ ቦታ ቢሄዱና ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ጓደኛ ለሆነ ሰው የቤታቸውን ቁልፍ ቢሰጡት፣ ጊዜው ሲደርስ ሊቀበሉት መምጣታቸው አይቀርም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት የሚቻልበት አንድ መንገድ ብቻ መኖሩን መጽሐፍ ቅዱስ ቢናገርም የድርሳኑ አዘጋጆች ግን እንዴት ሲኮን? ሌላም የመግቢያ መንገድ አለ ይላሉ፡፡ ከዚህ የተነሣ በመጽሐፋቸው ውስጥ ከአንድ በላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያወርሱ መንገዶች (ማርያም እና ሐና) መኖራቸው ቢታወጅም በዚህ ስፍራ ግን ከማርያም ጋር በተያያዘ የሰፈረውን እንመልከትና ሌላውን ደግሞ በቦታው እንደርስበታለን፡፡

---

[74] ኤፌሶን 2፥14-15፡፡
[75] ኤፌሶን 2፥17፡፡
[76] ኤፌሶን 2፥13፤ ገላትያ 1፥8-9፡፡

> ...የመንግሥተ ሰማይ ቁልፍ የሆንሽ ማርያም ሆይ ደስታ ይገባሻል፡፡ የአዳም ልጆች የነጻነት በዓላቸው ትሆኚ ዘንድ የተገባሽ ማርያም ሆይ ደስታ ይገባሻል በምድራውያንና በሰማያውያኑ መካከል አስታራቂ ለመሆን የተገባሽ ማርያም ሆይ ደስታ ይገባሻል...፡፡[77]

የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ ማርያም ናት የሚለው ሐሳብ ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር አይስማማም፡፡ ምክንያቱም «... ጌታ ተሰቅሎ ሳለ ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ ብሎ ቀዳሚ ሆኖ እንዲገባ ያደረገው ከእርሱ ጋር[78] የተሰቀለውን ወንበዴ እንደ ሆነ ይታመናል፡፡ ‹ጌታችን ከእነ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ኢዮብ፣ ዳዊት ነቢያት ሁሉ አስቀድሞ ገነት እንዲገባ ያደለው ፈያታይ ዘየማን ሽፍታና ወንበዴ የነበረውን፣ ከወንጀለኛነቱ ብዛት የተነሣ ለእስረኞች ምሕረት በሚደረግበት በአይሁድ ፋሲካ ቀን የተሰቀለውን ከፉ ወንበዴ ነው፡፡›[79]

መተርጉማንም ለሉቃስ 23÷43 በሰጡት የአንድምታ ትርጓሜ ላይ ‹አንተ ትቀድሞ ለአዳም አቡከ በዊአ ውስተ ገነት - ወደ ገነት በመግባት አባትህን አዳምን ትቀድመዋለህ› ብሎ ጌታ ስለ እርሱ አስቀድሞ መናገሩን ጽፈዋልና፡፡[80] ጌታ እንዲህ ብሎ ስለ መናገሩ ርግጠኛ መሆን ባይቻልም አዳምና ሔዋን ከገነት ከተባረሩ በኋላ ወደ ገነት ትገባለህ ተብሎ የተነገረለት መሆኑን ግን የተሰጠው ትርጉም ያረጋግጣል»፡፡[81] ይህ ማለት ደግሞ የመንግሥተ ሰማያት ቁልፍ የጌታ ደም እንጂ ማርያም አይደለችም ማለት ነው፡፡

ከላይ የድርሳኑ ጸሐፊዎች በተናገሩት ክፍል የጠቀሱት አንዱ ነገር ማርያም በምድራውያንና በሰማያውያኑ መካከል አስታራቂ ለመሆን የተገባት መሆኗን የሚናገር

---

[77] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሐሙስ ቍጥር 13 ገጽ 69፡፡

[78] በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ወንበዴው በቀኙ በኩል የተሰቀለው ነው ይባላል፡፡ ምን አልባትም ቀኝ የኃይልና የመልካም ነገር መገለጫ ስለሆነና በባህላችም *«በቀኝ ያውልህ»* የሚል ቡራኬ ስላለ ከዚህ በመነሣት ሊሆን ይችላል እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ *‹ተዘከረኒ በውስተ መንግሥተከ›* ያለው የትኛው እንደ ሆነ አይናገርም፡፡

[79] ያረጋል አበጋዝ (ዲያቆን)፣ መድሎተ ጽድቅ (ዐዲስ አበባ፣ 2007) ገጽ 345፣ 343፡፡

[80] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው (ዐዲስ አበባ፣ 1988) ገጽ 432፡፡

[81] ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ ሰማንያ አሐዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን (2012 - አራተኛ ዕትም) ገጽ 96፡፡

ነው፡፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዐዲስ ኪዳን መካከለኛና አስታራቂ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሚናገረው እውነት ጋር የሚጋጭ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ «የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ... ደርሳችኋል» (ዕብራውያን 12፥24) እና «የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የዐዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው» (ዕብራውያን 9፥15) እንዲሁም «እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፣ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ከራሱ ጋር እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና» (ቈላስይያስ 1፥19-20፤ ሮሜ 5፥10-11) ከሚለው የእግዚአብሔር ቃል ፈጽሞ የሚቃረን ነው፡፡ ይህም የክርስቶስን ክብርና ግብር እየወሰዱ ለፍጡራን በመስጠት ነገረ መለኮትን ማዛባትና ሰዎችን ወደ ስሕተት መምራት የተለመደ የድርሳናትና የገድላት ጸሐፊዎች ግብር መሆኑን ያሳያል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

## ስማችን በዓለም ለምን አልታወቀም?

ቅዱሱ መጽሐፍ እንደሚያስተምረው የእግዚአብሔር ሰዎች ራሳቸውን «ትል»፣ «ባሪያ»፣ «ጭንጋፍ» እያሉ ሲጠሩና «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» እያሉ ለጌታቸው ክብር ሲሰጡ እንጂ ራሳቸውን ከፍ ከፍ ለማድረግና በዓለም ላይ ዝነኛ ለመሆን ሲጥሩ አልታዩም፡፡[82] ይሁንና የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች ግን ከዚህ የተቃረነ መልእክታቸውን እንዲህ ሲሉ ያስነብባሉ፤

> ....[ሐና እና ኢያቄም] ጌታችን አምላካችን ንጉሣችን አዳኛችንና ፈጣሪያችን አቤቱ እያሉም ሰገዱ፡፡ እኛ አንተ ያከበርኸን ከፍ ከፍ ያደረኸን ክቡራን ነን፡፡ የዓለም መድኀኒት አንተን የወለደች /ማርያምን/ በመውለዳችን ስለምን ስማችንን በዓለም ሁሉ የተሰማና የታወቀ አላደረግኸውም? ስማችንን የታወቀ ብታደርገው ኖሮ መታሰቢያችንን በዓላችንን ባደረጉልን ነበር፡፡ ለሰማዕታት፣ ለመላእክት ለጻድቃንና ለደናግል በፊትህ ሞገስን ላገኙት ሁሉ እነሆ መታሰቢያቸውን ሲያደርጉ እናያለንና፡፡ አቤቱ ሆይ መታሰቢያችንን ለሚያደርግ ሰው ሞገስን ሰጠው፡፡

[82] መዝሙረ ዳዊት 22÷6፤ ሉቃስ 1÷48፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15÷8፤ ዮሐንስ 3÷30፡፡

> <u>በስማችን ምጽዋትን የሚሰጥ ሰው በአንተ ዘንድ ዋጋው ምንድን ነው? አሉት፡፡ መታሰቢያችሁን ያደረገ በስማችሁ ቤተ ክርስቲያናችሁን ያነፀ፣ የገድላችሁን መጽሐፍ የጻፈ እኔ በሚመጣው ዓለም አስደስተዋለሁ፡፡ ኀጢአቱንም ሁሉ አጠፋለታለሁ፤ የበደሉን ደበዳቤም እደመስሳለሁ አለ</u>፡፡[83]

ጸሐፊዎቹ በዚህ መልእክታቸው መሠረት ከዚህ በታች ያሉትን ስሕተቶች ሠርተዋል፤

1. ስለ ምን ስማችን አልታወቀም?

እንዲህ ያለውን ጥያቄ ያቀረቡት የእርሱ ስለመሆናቸው ወይም በእርሱ በማመናቸው ሳይሆን ማርያምን በመውለዳቸው መሆኑ ሐሳባቸው ምድራዊ (ዝና ፍለጋ) ምክንታቸውም ሥጋዊ (የእከሌ እናት ነኝ'ኮ የሚል) መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህም የተነሣ «ስለምን ስማችንን በዓለም ሁሉ የተሰማና የታወቀ አላደረከውም?» የሚል ምድራዊ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ በርግጥም ግን ጸሐፊው እያስተዋወቃቸው ያሉት ሰዎች መንፈሳዊና እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ናቸውን? ቢሆኑ ኖሮ እንዲህ ያለውን «እኔ» «የእኔ» የሚል ጥያቄ ያቀርቡ ነበርን? በፍጹም፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር፣ የልጁም የጌታ የኢየሱስ አገልጋዮች ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉና ክብርን ከጌታቸው እንጂ ከምድራውያን የሚፈልጉ ባለ መሆናቸው ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ በድርሰቱ ውስጥ ኢያቄምና ሐና የተባሉትም እንዲህ ዓይነት ጥያቄ በፍጹም አያቀርቡም፡፡

2. በዓላችንን ባደረጉልን ነበር

«አንተ ታዋቂ ስላላደረከን ነው እንጂ ብታደርገን ኖሮ ታዋቂ በሆንን ነበር» የሚለው ይህ የሐናና የኢያቄም ንግግር አንተ ጥፋተኛ ነህ እኛንም በድለኸናል ብሎ እግዚአብሔርን የሚከስና የሚወቅስ ነው፡፡ እንደ እነርሱ ሐሳብ እርሱ ታዋቂ ቢያደርጋቸው ሰዎች በዓላቸውን ያደርጉላቸው ነበርና፡፡ ይህም በቅዱሳኑ የተለመደ ጥያቄ አይደለም፡፡

[83] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሐሙስ ቍጥር 17-18 ገጽ 71-72፡፡

3. ሲያደርጉ እናያለንና

ቀደም ሲል እንዳቀረበው እግዚአብሔር ታዋቂ ስላላደረጋቸው ነው እንጂ ለሌሎች የሚደረገውም ለእነሱም አይቀርባቸውም ነበር፡፡ ለሌሎች የሚደረገው ምን እንደ ሆነ እንዲህ በሚል አቅርበውታል፡- «ለሰማዕታት፣ ለመላእክት፣ ለጻድቃንና ለደናግል በፊትህ ሞገስን ላገኙት ሁሉ እነሆ መታሰቢያቸውን ሲያደርጉ እናያለንና»፡፡ ይህ ንግግር «እኛ ግን…» የሚል መንፈስ ሲኖረው ለእነርሱ ተደርጎ ለእኛ ለምን ቀረ? ከሚል ቅናት የተወለደ ንግግር ነው፡፡ ይህም ከላይ እንዳነሣሁት በእግዚአብሔር ሰዎች ዘንድ ያልተለመደ ድርጊት ነው፡፡

4. በስማችሁ… አስደስተዋለሁ

ጌታ ቃል ገባላቸው ለማለት የሰፈረው ንግግር የመጣው በሌሎች ቅዱሳን መቅናታቸውን ከተናገሩ በኋላ ሲሆን ጌታም ደግሞ በእነርሱ ስም ቤተ ክርስቲያን ያነጸ እና የገድላቸውን መጽሐፍ የጻፈን እንደሚያስደስተው ገለጸ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደስታ ስለምናገኝበት ሁኔታ የሰፈረው ይህን ስላደረክ ወይም እንዲህ ስለ ሠራህ ባይባልም «…መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ» የሚል መሆኑ ሰማያዊውን ደስታ ለሚናፍቁ ሰዎች ምንኛ እርካታ ይሰጠ ይሆን?[84] ለእነዚህ የድርሳን አዘጋጆች ግን የደስታ ምንጭ በሕይወት መዝገብ (በሰማያት) መጻፍ ሳይሆን የሰው ታሪክ (ገድል) በመጻፍና በሰውዬው ስም ሕንፃ በመገንባት እንደ ሆነ አድርገው ማቅረባቸው ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ቃል ምን ያህል እያራቁት እንደ ሆነ ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

5. ኀጢአቱን ሁሉ አጠፋለታለሁ

ቤተ ክርስቲያን «ኀጢአትን የምትደመስስ» ብላ የምታምነው ክርስቶስ ኢየሱስን ነበር፡፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነትና ትምህርት ነው፡፡ ዘመን የወለደቸው መናፍቃን ግን ዘመን በወለደው ትምህርታቸው ዐዲስ ኑፋቄ እያሰራጩ ይገኛሉ፡፡ ይሄውም ክርስቶስ የከፈለውን ዋጋ፣ ያፈሰሰውን ደም ቸል ብሎ የእነ እከሌን መታሰቢያ ያደረገ ወይም ገድላቸውን የጻፈ፣ ያስጻፈ … ኀጢአቱን እምረዋለሁ ብሏል እያሉ የመጽሐፍ ቅዱሷ ቤተ ክርስቲያን የማታውቀውን ትምህርት እያስተማሩ

[84] ሉቃስ 10፥20፡፡

ይገኛሉ፡፡ ይህም «የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቈጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?» ተብሎ የተጻፈውን ቅዱስ ቃል መዘንጋት ነው፡፡[85]

## የምልጃው ሰንሰለት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምልጃ ሲናገር በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል ያለው አንድ እርሱም ክርስቶስ እንደ ሆነ ነው የሚያሳየው፡፡[86] ቅዱሱ መጽሐፍ አስረግጦ የሚያስተምረውን ይህን እውነት መቀበል የከበዳቸው ብዙዎች የየራሳቸውን አማላጅ ፍለጋ ብዙ ደክመዋል፡፡ የድካማቸውን ያህል ልባቸውን የሚያሳርፍላቸው ስላላገኙም የአማላጆቻቸው ብዛትና የምልጃው ሰንሰለት ቅጥልጥልነት ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ ይታያል፡፡

በፊት በፊት ወደ አማላጁ (ለምሳሌ ወደ ማርያም) መጸለይና በዚያም በኩል የሚፈለገው ነገር እንደሚገኝ ይታመን የነበረ ሲሆን አሁን አሁን ግን እሱ በቂ ሆኖ ስላልተገኘ ወደ አማላጁ (ወደ ማርያም) የሚያቀርብ ሌላ አማላጅ እያስፈለገ ይገኛል፡፡ ይህንም መጽሐፉ እንደሚከተለው ያስነበባል፤

> <u>ብፅዕትና ቅድስት የሆንሽ ሐና እና ቅዱስ ኢያቄም መታሰቢያቸው ለሚያደርግ ሰው ወደ እመቤታችን፣ አምላክን ወደ ወለደች ወደ መድኀኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ይለምናሉ፡፡ በእርሱ ላይ ፍርድ በተፈረደበት ጊዜም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተወደደው ልጇ በጌታችን ፊት ትቆማለች፡፡ የአባትና የእናቷን የኢያቄምንና የሐናን መታሰቢያ ለሚያደርጉትም ትለምንላቸዋች፣ ኀጢአታቸውንም ሁሉ ታስተሰርያለች፣ ወደ ዘላለም ሕይወትም ትመራቸዋለች፡፡ እንደዚሁም ሁሉ በምንተማመንበት ጸሎቷ</u>

[85] ዕብራውያን 10፥29፡፡
[86] 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፥5፡፡

> ሁላችንንም የመንግሥተ ሰማያትን መንገድ ትምራን፡፡ ከጥፋት ሞትም ታድነን፤ ለዘላለሙ አሜን፡፡[87]

በዚህ መጽሐፍ ሐሳብ መሠረት፤

ኀጢአተኛው (የሚጸልየው ሰው)

↓

ወደ ኢያቄምና ወደ ሐና፤ ኢያቄምና ሐና

↓

ወደ ማርያም፤ ማርያም ደግሞ

↓

ወደ ክርስቶስ

ይጸልያሉ፡፡ ይህም የምልጃው ሰንሰለት ርዝመት አማላጅ ለማግኘት ሌላ አማላጅ እየጨመረ መምጣቱንና ከበፊትም ይልቅ በፍጡር ላይ ያለው ጥገኝነት መጠንከሩን ያሳያል፡፡ ቀደም ሲል እንደተባለው ወደ ፍጡር ጸልየን ያ! ፍጡር ወደ ፈጣሪ ያስጠጋናል ይል የነበረው ትምህርት አሁን ደግሞ ከፍጡር ወደ ፍጡር የምንጠለጠል ደካማ ፍጡራን አድርጎናል፡፡

በአንድ በኩል ማርያምን የላቀች ለማድረግ ሌሎች ወደ እሷ፣ እሷ ደግሞ ወደ ጌታ እንደምትጸልይ ሊያሳዩን ይሞክራሉ፡፡ በዚህም አማላጅ ነው የሚሉንን አካል መልሰው ተማላጅ ሊሆን እንደሚችል እየነገሩን ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፤

> አማላጅ ማለት በሁለት አካላት መካከል ገብቶ አንዱ ለሌላው ምሕረት ይቅርታና ቸርነት እንዲያደርግ የሚለምን ማለት ነው፡፡ በዚህ ደገኛ ተግባር ውስጥ የሚሳተፉ ወገኖች ሦስት ሲሆኑ እነርሱም፤ የሚለምን፣ የሚለመንለት እና የሚለመን ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር አማላጅ፣ የሚማለድለት እና ተማላጅ ብሎ መፍታት ይቻላል፡፡ እነዚህ ሦስት አካላት በመንፈሳዊው ዓለም የየራሳቸው ግብር እና ድርሻ አላቸው፡፡ አንዱ በአንዱ ኃላፊነት

[87] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሐሙስ ቍጥር 20 ገጽ 73-74፡፡

> እና ድርሻ ውስጥ በኃይል አይገባም፡፡ በሌላ አነጋገር ተማላጁ አማላጅ ወይም ማላጁ ተማላጅ ሊሆን አይችልም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን የሚለመንለት ሰው በትክክለኛ የንስሐ ሕይወት ውስጥ ሲያልፍ ወደ አማላጅነት ሊሸጋገር ይችላል፡፡[88]

በማለት አማላጅ የሆነ ተማላጅ እንደማይሆንና እንዲህ ያለ የስልጣን እድገት እንደማይኖር ይነግሩናል፡፡ ይህም ትምህርታቸው የረጋ ነገር የሌለውና በየጊዜው ተለዋዋጭ መሆኑን በሚገባ ያሳያል፡፡ ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ የቅዱሳን ምልጃ የሚባለው ነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑ ነው፡፡

ሌላው የዚህ መልእክት ችግር የእናትና አባቷን (የኢያቄምንና የሐናን) ጸሎት ሰምታ ታማልደናለች የተባለችዋ ማርያም ወደ ልጇ ጸሎትን በማቅረብ ይቅር በላቸው ማራቸው ጸሎታቸውን ስማ... ማለት ሳይሆን «ኀጢአታቸውንም ሁሉ ታስተሰርያለች ወደ ዘላለም ሕይወትም ትመራቸዋለች» ተብሎ መጻፉ ሲሆን ይህም ሰይጣን የክርስቶስን ሥልጣንና ግብር ለመቀማት ምን ያህል ጥረት እያደረገ እንደ ሆነ ለማስተዋል ይረዳል፡፡ በእነዚህ ሰዎች ትምህርት እንደሚታየው፣ ቀደም ሲል አንዳንድ አስተውሎት በጎደላቸው ሰዎች ማርያም ‹ኀጢአታቸውን ይቅር በልና ወደ ዘላለም ሕይወት ምራቸው (አስገባቸው)› እያለች ትጸልያለች እየተባለ ይነገር የነበረው በራሱ ችግር የነበረበት ትምህርት ተቀይሮ ከዚያ በከፋ ሁኔታ ኀጢአት የምታስተሰርይና ወደ ዘላለም ሕይወት የምታስገባ አምላክ (ባለ ሥልጣን) ተደርጋ መቅረቧ በክርስትና ትምህርት ውስጥ መሠረት የሌለው ኑፋቄ ነው፡፡

## ነፍስን ከባሕር የምታሻግረዋ ሐና

ጸሐፊው ሐናን ከባሕር የምታሻግር የሚላት በታንኳ አልያም በመርከብ ከአንዱ የባሕር ዳርቻ ወደ ሌላኛው ዳርቻ ስለምታሻግር አይደለም፡፡ እንደ ጸሐፊው ሐሳብ ከሆነ ከባሕር የምታሻግረው ነፍስን ሲሆን እሷን ደግሞ «የሕይወት መርከብ» ሲል ይጠራታልና ከባሕር ታሻግሪያለሽ ማለቱ ከፍርድ ነጻ ታወጫለሽ፣ የዘላለም ሕይወት

---

[88] ኃይለ ማርያም ላቀው (መምህር)፣ ሐውልተ ስምዕ (2004) ገጽ 187 - አጽንዖት የግል፡፡

እንዲያገኙ ታደርጊያለሽ ለማለት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ሐሳቡም እንዲህ ይነበባል፤ «...ነፍስን ከባሕር የምታሻግር የሕይወት መርከብ አንቺ ነሽ እልሻለሁ»፡፡[89]

በዚህ መልእክት መሠረት ከባሕር የምታሻግረዋ የሕይወት መርከብ ሐና ሆና ስትቀመጥ በሌላ በኩል ደግሞ «አማናዊቷ ሐመረ ኖኅ እመቤታችንም ከማየ ኀጢአትና ከጥፋት ማዕበል የዳንባት የሕይወት መርከብ፣ የዕረፍት ወደብ [ናት]...» የሚል ትምህርት አለ፡፡[90] በዚህ መሠረት ከባሕር መሻገሪያ የተባሉ ሁለት ሰው ሠራሽ መርከቦች (ሐናና ማርያም - እናትና ልጅ) አሉን ማለት ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደ ተባለው ሐና የምታሻግረን ተብሎ የቀረበው ወደ ዘላለም ሕይወት ነው፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ዘላለም ሕይወት እንደ ተሻገርን የሚነገረን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ራሱ መድኀኒ ዓለም ክርስቶስ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም» ማለቱን መመልከቱ ምንኛ ልብን የሚያሳርፍ ነው፡፡[91]

እንግዲህ የክርስቶስን ንግግር እንደ ተራ ነገር ካልቈጠርነው በቀር አንደኛ መሻገሪያ ሐና (አያት)፣ ሁለተኛ መሻገሪያ ማርያም (እናት)፣ ሦስተኛ መሻገሪያ ኢየሱስ (ልጅ) በሚል እንድናስብ የሚያደርገን ምንም ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም ቃሉ የታመነ ስለሆነ የእሱ መሻገሪያነት ብቻ ለሁሉ በቂ ነው፡፡ በሌላ ቃል ከክርስቶስ ውጭ ያለው ሁሉ በክርስቶስ መሻገር የሚገባው በመሆኑ፣ ራሱን ማሻገር ባለ መቻሉ አሻጋሪ ያስፈለገው ፍጡር (ሰው) ለሌላ ሰው መሻገሪያ (አሻጋሪ) ለመሆን አይችልም፡፡

## የጻፈ ያስጻፈ ...

ገድላትና ድርሳናት በእጅ እየተገለበጡ ይባዙ፣ ይነበቡና ለትውልድ ይተላለፉ በነበረበት በቀደመው ዘመን የመጻፍና የማንበብ ችሎታ ያላቸው ጥቂቶች ነበሩ፡፡ እነርሱም ቢሆኑ በቤተ ክህነት አካባቢ የሚገኙ በመሆናቸው ብዙዎቹ መንፈሳዊ ነገር

89 ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሐሙስ ቍጥር 21 ገጽ 74፡፡

90 አንዱ ዓለም ዳግማዊ (መምህር)፣ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት (ሚያዝያ 1998) ገጽ 44፡፡

91 ዮሐንስ 5፥24፡፡

ላይ ትኩርት ያደረጉ ናቸው፡፡ ይህም ለአዋልድ መጻሕፍት መብዛትና ማበብ የበኩሉን አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡

እነዚህ ሰዎች እከሌ ተገለጠልኝ፣ እንቶኔ በራእይ ታየችኝ ወዘተ. በማለት የሚጽፉት ገድል ወይም ድርሳን አልያም ተኣምር... በዚያው በእነሱ ዘመንና አካባቢ ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር በማሰብ ይህን... የጻፈ፣ ያስጻፈ.... የሚሉትን መሠረተ ቢስ ብልጠት ለመጠቀም ሞክረዋል፡፡ የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጅም ተመሳሳይ መንገድ በመጠቀም፤ «አምላክን የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን የወለደቻት የተቀደሰችና ለቅድስና የተመረጠች የሐናን ዜና የምትናገር ይህችን መጽሐፍ የጻፈውን በብዙ ትጋትና ንቃት ያስጻፈውን ሰው ሰም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማይናወጥና በማይወድቅ የወርቅ ዐምድ በሚያበራና በሚያንጸባርቅ በወርቅ ቀለም ስሙን ይጻፍ፡፡ የጽድቅ ጌታን ፈቃድ ያደረጉ ምእመናን በተሰበሰቡበት ቦታም የሚያንጸባርቅ የሰርግ ልብስን ለብሶ በጸሎቷም ተውቦ በደስታ እየሳቀ በመካከላቸው ተሰብሳቢ ሆኖ ይቀመጥ፡፡... በሐና ጸሎት የልጇ ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዕዳ ደብዳቤውን ይደምስስለት፣ ይቅደድለትም፡፡ በማይሻርና በማይናወጥ ጌትነቱም ከእርሷ ጋር በቀኝ መቆም ያድለው» ይላል፡፡[92]

በዚህ ስፍራ ደግሞ ድርሳኑን የጻፈ ወይም/እና ያስጻፈ እነዚህ ጥቅሞች ያገኛል፤

1. በወርቅ ቀለም ስሙን ይጻፍ - ማለትም ወደ ዘላለም ሕይወት ይግባ፡፡
2. የሰርግ ልብስ ለብሶ የጌታን ፈቃድ ባደረጉ ምእመናን መካከል ይቀመጥ - ማለትም ወደ ዘላለም ሕይወት ይግባ፡፡
3. የዕዳ ደብዳቤው ይደመስስለት፣ ይቀደድለትም - ማለትም ወደ ዘላለም ሕይወት ይግባ፡፡
4. ከእርሷ ጋር በጌታ ቀኝ መቆምን ያድለው - ማለትም ወደ ዘላለም ሕይወት ይግባ፡፡

የሚገርመው ይህ ሁሉ የተባለው ዋጋ በከፈለለት በክርስቶስ በማመኑ፣ ወይም ኀጢአተኛነቱ ተሰምቶት ንስሐ በመግባቱ፣ ወይም ጻድቅ ፈራጅ ወደ ሆነው አምላክ በመጠጋቱ ሳይሆን መጽሐፉን በመጻፉ ወይም/እና በማስጻፉ ነው፡፡ በጣም የሚያሳዝነው የተባሉትን የተስፋ ቃሎች ለማግኘት የሚታደሉትና የየድርሻቸውን

[92] ተስፉ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሐሙስ ቊጥር 23 ገጽ 75-76፡፡

የሚያገኙበት ጥቂቱ የመጀመሪያዎቹ መጻፍና ማንበብ የሚችሉትና ከእነርሱ ሲያልፍ ደግሞ ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ነገር ግን ገንዘብ ከፍለው ለማስጻፍ አልያም ለማስነበብ እድል ያላቸው ሲሆኑ ከእነዚህ ከሁለቱ ውጪ ያሉ ምስኪናን (ማንበብና መጻፍ የማይችሉና ገንዘብ የሌላቸው) ግን ከተስፋ ቃሉ ሽርፍራፊ እንኳ የማይደርሳቸው መሆኑ ነው፡፡

እንደ ደራሲው አስተሳሰብ መጽሐፍ መጻፍና ማስጻፍ፣ ማንበብና ማስነበብ የዘላለም ሕይወትን የሚያስገኝ ቢሆን ከወንጌላት የተሻለ ሌላ መጽሐፍ ስለሌለ (ሁሉም መጻሕፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ልጆች ናቸው ተብሎ የሚታመን በመሆኑ) እርሱን እየጻፍንና እያስጻፍን የዘላለም ሕይወት ተካፋዮች በሆን ነበር፡፡ ለጌታም እስከ መስቀል በሚደርስ መከራ ውስጥ ከማለፍ ይልቅ የሚቀለው መጻሕፍቱን «ጻፉ፣ አስጽፉ፣ አንብቡ፣ አስነብቡ» የሚለው ነበር፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን «ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል» በማለት ሕይወት የሚገኘው በመጻፍ ወይም በማስጻፍ ሳይሆን በማመን መሆኑን ስለ ሆነ የእነዚያ የድርሳናትና የመሳሰሉት መጻሕፍት ጸሐፊዎችን አሳሳች የፈጠራ ትምህርት ከመስማትና ከእግዚአብሔር ቃል ከመራቅ መጠንቀቅ ይገባል፡፡[93]

## ተራሮች ኀብስት ባሕሩም ወተትና ማር ሆኑ

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረው በእግዚአብሔር እጅ የተለያዩ ድንቅ ድንቅ ነገሮች ተከናውነዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ከምንም ነገር ሰማይንና ምድርን ከመፍጠር በላይ ምን ድንቅ ነገር አለ? ይህን ላደረገ አምላክም፤

- ውሃን ወደ ደም መቀየር፣
- አህያን ማናገር፣
- የሞተን ማስነሣት፣
- ባሕር መክፈል፣
- ፀሐይን ማቆም ... ምንኛ ተራ ነገር ነው፡፡

እርሱ የተኣምራት አምላክ ነውና እርሱ ላይ እንጂ ተኣምራት ላይ ትኩረት እንዳናደርግ አጠነክሮ መክሮናል፡፡ ምክንያቱም ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች

93 ዮሐንስ 20፥31፡፡

ነቢያት «የተመረጡትን እንኳ ያስቱ ዘንድ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ[ና]»፡፡[94] ስለዚህ ተኣምራት ቢታይና ተደረገ ተብሎ ቢነገር ተአምሩ ከማን እንደ ሆነ መመርመርና በተከናወነው ተአምር ላይ ሳይሆን እምነትን ተአምሩን ባደረገው ጌታ ላይ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም በሙሴ ፊት በትርን ወደ እባብነት የለወጠ ጥንተ ጠላታችን ዛሬም ሰዎችን ለማሳሳት ከዚህ የሚበልጥ ተአምር ሊያደርግ እንደሚችል ስለ ተነገረን ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ እነዚያ የድርሳን አዘጋጆች የተደነቁበትን ተኣምር እንዲህ አስነብበዋል፤

«ንጉሥ ክርስቶስን በወለደች ጊዜም ተራሮች የሕይወት ኅብስት ሆኑ፡፡ ኮረብታዎችም የበረከት ፍሬን አፈሩ፡፡ የባሕሩ ውሃም ወተትና ማር ሆነች፡፡ በዚህች ቤትም ስለት በሆነ የኀጢአት ሰይፍ ብዙ ሰዎችን የሚነድፉ የበሽታ መናፈስት አይኖሩም…»፡፡[95]

ጸሓፍቱ ይህን ለምን እንዳደረጉ ግልጽ ባይሆንም ይህን «ተኣምር» ያገኙት ከየት ይሆን? የሚል ጥያቄ መነሣቱ ግን የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም ክስተቱ የተከናወነ ቢሆን ኖሮ (ደራሲው ተከናወነ ያለን ክርስቶስ ሲወለድ ነውና) በጌታችን መወለድ የተከናወኑ ነገሮች ማለትም፡-

- ኮከቧ እየመራች ጌታ የተወለደበትን ቦታ መጠቆሟ፣
- ለእረኞች የምሥራች የሚል መልእክት በመላእክት መምጣቱ፣ እና
- መላእክትና የሰው ልጆች አብረው እግዚአብሔርን ማመስገናቸው

በተመዘገቡበት በወንጌላት አልያም ከመልእክታት በአንዱ ውስጥ ባገኘው ነበር፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ተራሮች እና ኮረብቶች መብል፣ ባሕሩም የሚጠጣ ሆነ የሚል ከሰው አእምሮ የፈለቀ እንግዳ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን ሁሉም ሰው ሊረዳው ይገባል፡፡ ጸሐፊው እንደሚለው፣ ጌታ በተወለደ ጊዜ እንዲህ ያለ ተኣምር ሆኖ ቢሆን አይሁድ ሲጠብቁት የነበረው መሲሕ መምጣቱን አምነው ለመቀበል ባልተቸገሩም ነበር፡፡

---

[94] ማቴዎስ 24፥24፤ ማርቆስ 13፥22፡፡
[95] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘቀዳሚት ቍጥር 12 ገጽ 94-95፡፡

# የማርያም ንጽሕና

መጽሐፍ ቅዱስ ከፍጥረት ወገን እከሌ ንጹሕ ነው፣ አንቶኔ ደግሞ ያለ እንከን ይገኛል የሚል ትምህርት የለውም፡፡ አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎችን «ጻድቅ» እያለ ቢጠራም ይህ ስያሜ ከነበሩበት ማኅበረሰብ አንጻር መታየት የሚገባው ነው፡፡ ለምሳሌ ከእነዚህ «ጻድቅ» ከተባሉ ሰዎች መካከል ከብሉይ ኪዳን አንድ ከዐዲስ ኪዳን አንድ ወስደን እንመልከት፤

1. ኖኅ (ዘፍጥረት 6፥9)፣
2. ዘካርያስና ኤልሳቤጥ (ሉቃስ 1፥5)፡፡

ቀደም ሲል እንደ ተባለው የእነዚህ ሰዎች ጽድቅ መታየት ያለበት በዘመናቸው ከነበሩት ሰዎች ተሸሎ ከመገኘት አንጻር ነው፡፡ ምክንያቱም ጻድቅ ተብለው የተጠሩት እነዚህ ሰዎች ድካም ውስጥ ገብተው የሚገኙበት ጊዜ ትንሽ አይደለም፡፡

ከዚህም ሌላ ሁሉም ሰው «በአንዱ በአዳም» በደል ተጠያቂ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እንዲህ ባይሆን ኖሮ የሁለተኛው አዳም መምጣት ባላስፈለገ ነበር፡፡ ምናልባት ከፍጥረት ወገን ንጹሕ የሆነ አንድ ሰው ቢገኝ የዓለም ታሪክና የፍጥረት ሁኔታ በተለወጠ ነበር፡፡ ምክንያቱም አዳም ሲፈጠር ንጹሕ የነበረ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውም ግንኙነት መልካም ነበር፡፡ ይህ ግንኙነት የተበላሸው አዳም በበደለ ሰዓት ነው፡፡ አዳም ሲፈጠር በነበረበት የንጽሕና ደረጃ ላይ የሚገኝ ሌላ ሰው ቢኖር ምናልባትም እግዚአብሔር በዚህ ሰው አማካይነት የዓለምን ታሪክ በቀየረ ነበር፡፡

የድርሳኑ አዘጋጆች ቅድስት ማርያምን በተመለከተ «<u>ከሰው ወገን እንደ እመቤታችን በንጽሕና[96] የሚገኝ ማን ነው?... በኅሊናዋም፣ በሥጋዋም፣ በነፍሷም ንጽሕት እንደ</u>

[96] ከዚህም በተጨማሪ «... ንጽሕት በሆነች በሚስቱ ማሕፀን የመፀነሷን ነገር መልአኩ ለአባቷ እንደነገረው መካን በሆነች በሐና ማሕፀን ተጸነሰች» በማለት የምን ማርያም ብቻ ሐናም ብትሆን ምንም የለባትም የሚልም ጨምረዋል (ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘዓርብ ቍጥር 9 ገጽ 82)፡፡ በዚህ ደግሞ አንድ ብቻ ሳይሆን ሁለት ንጹሕ የሆኑ ሰዎች እንዳሉን አመላክተዋል፡፡ ምናልባት ወደ ፊት ደግሞ ሦስት ዐራት እያለ ይቀጥል ይሆናል፡፡

ሆነች እንደ እመቤታችን ማርያም መላእክት እንኳ ፈጽመው አይመስሏትም...» የሚል ነገር አስነብበዋል፡፡[97]

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እንደመሆናችን እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ በመሆኑ ነገሮችን ከእርሱ በመነሣት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ስለ ንጽሕና ሲናገር የኢየሱስን ንጽሕና ብቻ ነው የሚያውጀው፡፡ ከእርሱ ውጪ በኅሊናም፣ በሥጋም፣ በነፍስም ንጹሕ ሆኖ ለመመስገን የሚችል ሰው የለም፡፡

ቅዱሱን መጽሐፍ የጻፉት ወንጌላውያንና የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት አሁን ላይ ቅድስት ድንግል ማርያም እንዲህ ናት እንዲያ ናት ከምንለው ይልቅ ለእርሷ ቅርብ ሰዎች ነበሩ፡፡

- በቃና በነበረው ሰርግ ላይ ደቀ መዛሙርቱና እናቱ አብረው ነበሩ፣[98]
- ለጸሎት አብራቸው ትተጋ ነበር፣[99]
- በአደራ የተሰጠችውም ከደቀ መዛሙርቱ መካከል የወደው ለነበረው ለዮሐንስ ነበር፡፡[100]

ነገር ግን በእነዚህ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርትና ተከታዮች በተጻፉት 27 የዐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለ ማርያም ከሰው ዘር ሁሉ የተለየ ቅድስና መናገር ቀርቶ ፍንጭ የሚሰጥ እንኳ ያለ መኖሩ አስገራሚ ነው፡፡

በተለይም ከሃያ ሰባቱ መጻሕፍት ውስጥ አምስት መጻሕፍት፣ (አንድ ወንጌል፣ ሦስት መልእክታት፣ አንድ ራእይ) የጻፈው ወንጌላዊው ዮሐንስ ማርያምን በአደራ ተቀብሎ ወደ ቤቱ እንደ መውሰዱ፣ ስለ ማርያም ብዙ ነገሮችን ሊሰማና ሊያውቅ የሚችልበት ዕድል ነበረው፡፡ አስገራሚው ነገር ግን ከአምስቱ መጻሕፍት ውስጥ በአንድ ስፍራ እንኳ ማርያምን በተመለከተ «የዘር ውርስ ኀጢአት የለባትም»፣ «ከሰው ወገን ንጽሕት ናት»፣ «ከመላእከት ወገን እሷን የሚመስል የለም»፣ «ታማልዳለች» ወ.ዘ.ተ የሚል አስተያየት አለመስጠቱ ነው፡፡

---

[97] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 21 ገጽ 17 - አጽንዖት የግል፡፡
[98] ዮሐንስ 2፡፡
[99] የሐዋርያት ሥራ 1፡፡
[100] ዮሐንስ 19÷19፡፡

ታዲያ አነጋገሪ የሚሆነው ከዮሐንስ ይልቅ ራሳቸውን የተሻሉ አድርገው ያስቀመጡ ሰዎች፣ «በራእይ ተገለጠችልን» በሚል ሽፋን ተከልለው የእግዚአብሔር ቃል የማያውቀውን የሰው ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን አሾልከው ሲያስገቡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በዝምታ መመልከታቸውና ምእመኑን ለሐሰተኛ ትምህርት ማጋለጣቸው ነው፡፡

መጽሐፈ ዲድስቅልያም፤ ‹‹... ስለ እኛ ሰው ከሆነው ከአንዱ ከእግዚአብሔር ቃል በቀር <u>አንድ ሰዓት እንኳ ያለ ኀጢአት የሚኖር ሰው</u> የለምና» በሚለው መልእክቱ ከድርሳነ ኢያቄም ወሐና ጋር እንደማይስማማ በይፋ ያውጃል፡፡[101] ይህም ቤተ ክርስቲያን ትምህርቷን መለስ ብላ እንድትመረምር ያነሣሣል፡፡ በዚህ በመጽሐፈ ዲድስቅልያ ሐሳብ ውስጥ አብሮ የተጠቀሰ አካል የሌለ መሆኑ ብቻ ሳይሆን «ከእግዚአብሔር ቃል በቀር» ለአንድ ሰዓት እንኳ ያለ ኀጢአት የሚኖር «ሰው» የለም በማለት የአዳም ዘር ሆኖ ኀጢአተኛ ያልሆነና የማይሆን እንደሌለ ያስተምራል፡ ፡ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ «ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ»[102] እያለ ከሚያስተምረው ጋር ይስማማል፡፡

## ከሴቶች ይልቅ ምስጋናሽ ይብዛ

ርዕስ ሆኖ የተቀመጠውን ሲመለከቱ፣ ‹ይህ ምስጋና ለማርያም ነው› ብለው አሰበው ይሆናል፡፡ እስከ ዛሬ በዚህ ዓይነት አገላለጽ «ምስጋና» ይቀርብ የነበረው ለማርያም ስለሆነ እንዲህ ማሰብዎ ከተለመደው አንጻር ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ምስጋና ለማርያም የቀረበ ባለመሆኑ ግምትዎ ስሕተት ነው፡፡ ስለዚህ መጽሐፉ ምስጋናውን ለማን እንደሚያቀርብ አብረን እንመልከት፤

> <u>... ጽኑ የሆንሽ ቅድስት ሐና ሆይ ከአንቺ በፊትም ከአንቺ በኋላም ከነበሩ ሴቶች ይልቅ ምስጋናሽ ምን ይበዛ? እንደ አንቺ ሞገስን አላገኙምና፡፡</u>[103]

---

[101] ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ መጽሐፈ ዲድስቅልያ (2004) አንቀጽ 6 ቍጥር 19 - አጽንዖት የግል፡፡

[102] ሮሜ 3፥11፤ 5፥12-14፡፡

[103] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 23 ገጽ 19፡፡

የአዋድ መጻሕፍት ጸሐፊዎች አንደ አዝማሪዎች አንዱን ምስጋና ለብዙ አካላት ማድረግ ልማዳቸው በመሆኑ በዚህ ልማዳቸው ምክንያት ከሴቶች ሁሉ ተለይታ ምስጋና የሚገባት ከዚህ ባስ ሲልም ከፍጥረት ሁሉ ተለይታ ምስጋና የሚገባት ማርያም ናት ሲሉ እንዳልነበሩ፣ አሁን ደግሞ «ከአንቺ በፊትም ከአንቺ በኋላም ከነበሩ ሴቶች ይልቅ» (ማለትም ከሴቶቸ ሁሉ) ምስጋናሽ ምን ይበዛ በሚል ባለተራ አበጅተዋል፡፡

ከፍጥረት ሁሉ ይልቅ ምስጋና የሚገባው የሰማይና የምድር ፈጣሪ ብቻ ነው፡፡ ቅዱሱ መጽሐፋችን «እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን»[104] ሲል በደባልነት ሊመሰገን የሚገባው ሌላ አካል ስለ መኖሩ አልነገረንም፡፡

# የመለኮት ሥጋ የተዋሐዳት

«ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም» የሚለውን አባባል እውነት የሚያደርጉ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ባይኖሩ አባባሉ በተዘነጋ ነበር፡፡ በምናባቸው ስለው እውነተኛ ሴት የሚያስመስሏት ሐናን እነርሱ ሊያስቀምጧት ያሰቡት የቅድስና ማማ ላይ ቢሰቅሏትም ውስጣቸው ስላልረካ፤ «...<u>ቅድስት ሃና ግን ሥጋዋ የመለኮት ሥጋ የተዋሐደው በመሆኑ ዳግመኛ ሞትን አላየችም</u>» የሚል መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ [105]

እንደምታዩት ይህ ጽሑፋቸው ደግሞ ሦስት ችግሮች አሉበት፤

1. ዳግመኛ አልሞተችም፤ ሐና ሞታ ነበር የሚል ሐሳብ ያለው ሲሆን በድጋሚ አልሞተችም ማለቱ ደግሞ ተነሥታለች የሚል ሐሳብ አለው፡፡ ነገር ግን መቼ ነው የተነሣችው? ከኢየሱስ በፊት ወይስ በኋላ? የተነሣችውስ በራሷ ኃይል ነው ወይስ ሌላ አካል ነው ያስነሣት? ድርሳኑ እነዚህን ነጥቦች በተመለከተ ምንም ፍንጭ የማይሰጥ በመሆኑ ለጥያቄው የሚኖረው መልስ ዝምታ ብቻ ነው፡፡
2. የመለኮት ሥጋ፤ በተደጋጋሚ የኢየሱስ አያት እየተባለች የምትጠራዋ ሐና በዚህ መጽሐፍ አማካይነት ደግሞ መለኮት የተዋሐደው የእሷን ሥጋ ነው እየተባለ

[104] መዝሙረ ዳዊት 150÷6፡፡
[105] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሰኑይ ቍጥር 24 ገጽ 20፡፡

ነው፡፡ ምናልባት ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ «ያዳነን የሐና ሥጋ ነው» የሚል ትምህርት እንሰማ ይሆናል፡፡

3. የሐና ሥጋ «የመለኮት ሥጋ የተዋሐደው» በመሆኑ እሷንም «ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ» ለማለት ይቻላል ማለት ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በዚህ መጽሐፍ መልእክት መሠረት «ቃል ሥጋ» የሆነው በሐና ነው ማለት ነው፡፡
4. የመለኮት ሥጋ፡- በዚህ ክፍል መለኮት ሥጋ እንዳለው ተደርጎ ቀርቧል፡፡ እስከ አሁን በሚታወቀው የክርስትና ትምህርት መሠረት መለኮት ረቂቅ፣ የማይታይና የማይዳሰስ መንፈስ ነው፡፡ የኦርቶዶክስ አስተምህሮም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ታዲያ ይህ «የመለኮት ሥጋ» የሚለው ኑፋቄ በመጽሐፏ ውስጥ ተዘንቆ መገኘቱ ምነው እረኛ የለም እንዴ? ማስባሉ አይቀርም፡፡ ይህንም ኑፋቄ እያዩ ዝም ማለትም ለሕዝብ ሕይወት ደንታ ቢስ መሆንና ከፍተኛ በደል ነው፡፡

ሌላው በደል ቀርቶ የጸሐፊውን የስሕተት ጥግ ምን ያህል የከፋ እንደ ሆነ የሚያሳየው ይህ ምንባብ ብቻ፣ ክርስቲያናዊውን አስተምህሮ ለመጠበቅና የሰው ልጆች ድኅነት ግድ ለሚለው ሰው ከእንደዚህ ዓይነቱ እንግዳ ትምህርት ራሱንና ወገኑን እንዲጠብቅ የማንቂያ ደወል ይሆናል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል፡፡

## ከሴቶች ሁሉ ተለይታ ብፅዕት ናት

በርዕሱ ላይ የተቀመጠውን ሲመለከቱ ማርያምን አስበው ከሆነ ተሳስተዋል፡፡ ታዲያ ለማን ነው? ካሉ «...<u>ሐና ግን ፈጽማ ትከብራለች ከሴቶች ሁሉ ተለይታ ብፅዕት ናትና፡፡ በአማላጅነቷ የሚተማመንም ብፁዕ ነው፡፡ በዕጣንና በቁርባን መታሰቢያዋን የሚያደርግም ብፁዕ ነው</u>» በማለት ማንነቷን ይናገራል፡፡[106]

1. ጸሐፊው «ከሴቶች ሁሉ» ለይቶ ሐናን ብፅዕት እንደ ሆነች ሲያስቀምጥ ከቀሪዎቹ ሴቶች ውስጥ ማርያምንም ማካተቱን አላስተዋለውም፡፡ በርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ማርያም «ከሴቶች **<u>መካከል</u>**» ብፅዕት እንደ ሆነች ያስተምራል፡፡ የድርሳኑ ጸሐፊ ግን ሐና «ከሴቶች **<u>ሁሉ</u>**» ለይቶ የብፅዕናን ካባ ይደርብላታል፡፡ በዚህ መሠረት ከማርያም ይልቅ የሐና ብፅዕና የላቀ ነው፡፡

---

[106] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘረቡዕ ቍጥር 4 ገጽ 44፡፡

2. ብፅዕት ሐና ብፅዕናዋ ወደ ሌሎችም በሁለት መንገድ ይወርዳል፡፡ የሐናን ብፅዕና ለመጋራት ግን በአማላጅነቷ መተማመንና በዕጣን በቁርባን መታሰቢያዋን የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡ ይህም ጸሐፊው እንግዳ የሆነ ትምህርት አስተማሪነቱን ያጋለጠበት መልእክት ነው፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ብፁዕ ናቸው ብሎ ከሚዘረዝራቸው መካከል በፍጡር አማላጅነት በማመንና በዕጣንና በቁርባን መታሰቢያ በማድረግ ብፅዕናን ያገኘ ማንም የለምና፡፡[107]

## የማያልቅ ሕይወት በኅብስትና በውሃ

የአዳም ልጅ በሙሉ በዚህ ምድር ሲኖር ፍፁም ጤንነት፣ ደስተኛ ሕይወትና ሰላማዊ ኑሮ፤ ከዚህ ዓለም ሲያልፍ ደግሞ የማያልቅ (የዘላለም) ሕይወት እንዲኖረው ይፈልጋል፡፡ ይህንም ለማግኘት ይሆነኛል በሚለው መንገድ ሁሉ ከመሄድ ወደ ኋላ አይልም፡፡ መልካም የሚመስለውንም ነገር ሁሉ ለመንካትና ለመቅመስ ይሞክራል፡፡ ታዲያ የሚያድን በሚመስል፣ ነገር ግን ባልሆነ መንገድ ላይ እንዲራመድ የስሕተት መምህራን ድርሻ የሚናቅ አይደለም፡፡ በዚህ የስሕተት ጎዳና ላይ ቆሞ ሰዎችን ወደ ጥፋት እየመራ የሚገኘው የድርሳነ ኢያቄም ወሐና ጸሐፊም፤

> ስለ ቅድስት ሐና ብሎ ኅብስትንና ቀዝቃዛ ውሃን የሚሰጥ ብፁዕ ነው፤ መቶ እጥፍ ያገኛልና፡፡ በዚህ ዓለም በሥጋው ይድናል በሚመጣው ዓለምም መልካም ዋጋን የማያልቅ ሕይወትን ያገኛል፡፡[108]

የሚል ትምህርት አቅርቧል፡፡ በዚህ የደራሲው «የተስፋ ቃል» መሠረት ሦስት «በረከቶች» ይገኛሉ፡፡

1. መቶ እጥፍ፤ ምድራዊ በረከትን የሚያመለክተው ይህ «የተስፋ ቃል» (ስለ ሐና ተብሎ የተሰጠው ኅብስትና ቀዝቃዛ ውሃ) በመቶ እጥፍ ተመልሶ እንደሚመጣ (በረከት እንደሚኖር) የሚያመለክት ነው፡፡ በምድራዊ በረከት ለመባረክ በሐና ስም ኅብስትና ውሃ መስጠት ጥሩ ከሆነ ድሆችን ሰብስቦ በየወሩ፤

---

[107] የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5፡፡

[108] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘረቡዕ ቍጥር 5 ገጽ 44-45፡፡

100 ኪሎ ዱቄት ማብላት ቢቻል
100 እጥፍ ቃል ኪዳን ተገብቷልና
የ10000 ኪሎ ወይም የ100 ኩንታል ዱቄት በረከት በየወሩ ይገኛል ማለት ነው፡፡

ይህን በአንድ ዓመት ብቻ ብናሰላው፤ 10000 ኪሎ በረከት x በ12 ወራት = 120000 ኪሎ ወይም የ1200 ኩንታል በረከት ይሆናል፡፡

ይህ ደግሞ በብሉይ ኪዳን እንደ ነበረው ያለ ምድራዊ በረከት ነው፡፡ በቀድሞው ኪዳን ሕግጋቱን መጠበቅና እንደ ፈቃደ እግዚአብሔር ለመመላለስ ጥረት ማድረግ በምድራዊ በረከት የሚያጠግብ ሲሆን በተቃራኒው መሆን ደግሞ ለቅጣት ይዳርጋል፡፡ «እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፣ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እንቢ ብትሉ ግን ብታምፁም፣ ሰይፍ ይበላችኋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና» ተብሎ እንደተጻፈው ማለት ነው (ኢሳይያስ 1፥19-20)፡፡

2. በሥጋው ይድናል፤ ምንም እንኳ የደራሲው «የተስፋ ቃል» ይድናል ቢልም ዳኙ የሚድነው ከምን እንደ ሆነ (ከመከራ፣ ከበሽታ ወይም ከፈተና) ግልጽ አይደለም፡፡ የሚያድነው ኅብስትና ቀዝቃዛ ውሃ መስጠት መሆኑ ደግሞ በዚህ መንገድ (ከሥጋ ችግርም ቢሆን እንኳ) መዳን የሚቻል መሆኑን የሚናገር የቅዱስ መጽሐፍ ድጋፍ ስለሌለ፣ የድርሳኑ ጸሐፊ ከየት እንዳመጣው የማይታወቅ የትምህርት አረም ነው፡፡

3. በሚመጣው ዓለም… ዋጋን… የማያልቅ ሕይወትን ያገኛል፤ መጽሐፍ ቅዱስ የማያልቅ (የዘላለም) ሕይወት የሚገኘው በክርስቶስ በማመን መሆኑን ሲያስተምር ከዚህ በተለየ መንገድ የዘላለም ሕይወት እንደሚገኝ ፍንጭ አይሰጥም፡፡[109] የዘላለም ሕይወት ሊገኝበት የሚችለውን አስተማማኙንና ብቸኛውን የእግዚአብሔር መንገድ፣ ሰዎች እንዳያዩትና በዚያም ወደ ዘላለም ሕይወት እንዳይገቡ አሳሳች መንገድ በማዘጋጀት ሰውን እያሳተ ያለውን ይህን መጽሐፍ አባቶች ተመልክተው የሚታረመውን ማረም የሚወገደውን ማስወገድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

[109] ዮሐንስ 3፥14-16፡ 36፤ 5፥24፤ ሮሜ 6፥23፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፥20፡፡

# ወደ እርሷ ለምኑ!

ቀደም ሲል መዛግብተ ቃላት ለጸሎት በሰጡት ትርጓሜ መሠረት፣ ሰውና እግዚአብሔር (ፈጣሪና ፍጡር) ከሚገናኙባቸው መንገዶች ዋነኛው ጸሎት ነው፡፡ ጸሎት «ኅብረትን፣ ምስጋናን፣ ስግደትን፣ ልመናን፣ ምልጃን» የሚያጠቃልል «አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገሩበት እርሱን የሚያመልኩበት፣ የሚያመሰግኑበትና የሚያወድሱበት እንዲሁም በእርሱ ፊት የሚናዘዙበትና ምሕረቱን የሚለምኑበት» መንገድ ነው፡፡[110] ከዚህ የተነሣ ሰይጣን የሁለቱን የግንኙነት መስመር በማዛባት ኅብረታቸውን ለማበላሸት ጸሎት ላይ ትኩረት ያደረገ ይመስላል፡፡

ከዚህ የተነሣ አንዳንዶች በድካም፣ ሌሎች በጊዜ ማጣት፣ ከዚህ ባስ ሲል ደግሞ በቸልተኝነት እንዲሁም ስለ ጸሎት ጥቅም ባለ ማወቅ ምክንያት እንደ ነገሩ የሚጸልዩ ሰዎች ቊጥር ቀላል አይደለም፡፡

ከዚህ ለየት ብሎ ደግሞ ‹እየጸለይን ነው› ብለው ነገር ግን ጸሎታቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ሰዎችም ብዙዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች እንዲሳሳቱ አስተዋጽኦ ካደረጉት (እያደረጉ ካሉት) ሰዎች መካከል የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች ይገኙበታል፡፡ ለዚህም ማሳያ እንዲሆን «... መታሰቢያዋን ማድረግም አትርሱ፤ በጨከነ ልቡናም ወደ እርሷ ለምኑ፡፡ እርሷም የኀጢአታችሁን ስርየት ታገኙ ዘንድ የልጇ ልጅ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ቃል ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስም ትለምንላችኋለች» እያሉ ያሰፈሩትን መመልከት ይቻላል፡፡[111]

ጸሐፊው «በጨከነ ልቡና» ወደ ሐና እንድንጸልይ ሲያበረታታን «ሥጋ ሁሉ ጸሎትን ወደምትሰማ ወደ አንተ ይመጣል»[112] የሚለውን ሕያው ቃል ስላላነበበው ይሆን? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ጸሐፊው ለምን «በጨከነ ልቡና» ወደ ሐና መጸለይ እንዳለብን ለማሳየት የሞከረውም ለኀጢአታችን ስርየት እንደምታስገኝልን በመግለጽ ነው፤ ይህ ደግሞ ከነገረ ድኅነት ትምህርት በተቃራኒ የቆመ ፍልስፍና ነው፡፡

---

[110] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (ዐዲስ አበባ፣ 1998 - ስምንተኛ ዕትም) ገጽ 264፡፡ ግሎባል የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት፣ ዐዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (2005 - ሁለተኛ ዕትም) ገጽ 571፡፡

[111] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘረቡዕ ቊጥር 6 ገጽ 45፡፡

[112] መዝሙረ ዳዊት 65፥2፡፡

እግዚአብሔር በገለጸው ዘላለማዊ ፈቃዱ መሠረት የኀጢአት ስርየት ያገኘነው በክርስቶስ ደም ብቻ ነው፡፡ ሐዋርያው «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» የሚለውን የጻፈው በልመና የሚገኝ ስርየተ ኀጢአት እንደሌለ መንፈስ ቅዱስ ስለ ገለጠለትና ስለ ተገነዘበ እንጂ፣ የሚቻል ቢሆን ኖሮ እንደ ድርሳን ጸሐፊዎቹ ለምናችሁ ወይም አስለምናችሁ ከኀጢአታችሁ ንጹ ማለት አስቸግሮት አይደለም፡፡[113]

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው «ኀጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች»፡፡[114] ምክንያቱም «የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና»፡፡[115] በዚህም ምክንያት በቀደመው ኪዳን እንኳ ስለ ሰው ኀጢአት እንስሳት ምትክ ሆነው ይሰዉ እንደ ነበር ማስታወሱ መልካም ነው፡፡ ለዚህ ነው ሐዋርያው «ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» ከማለቱ አስቀድሞ «አንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል» ያለው፡፡[116]

በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ፣ «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀድሱ ከሆኑ፣ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?» በማለት ስርየት ሊገኝ የሚለችው በደም እንደ ሆነ አስረግጦ እየተናገረ፣[117] በፍጡር ልመና የኀጢአት ስርየት ማግኘት ይቻላል እያሉ ማስተማር የክርስቶስን ደም ማቃለልና የሚገባውን ክብር መንፈግ ነው፡፡ እንዲህ ለሚያደርግ ሰው ደግሞ «እግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኵስ ነገር የቈጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፣ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?» ተብሎ እንደ ተጻፈ ማስተዋልና ገንዘብ ማድረግ ከእንደዚህ ዓይነት ሐሰተኛ ትምህርቶች ራስን ለመጠበቅ ይረዳል፡፡[118]

---

[113] ዕብራውያን 9፥22፡፡
[114] ሕዝቅኤል 18፥20፡4፡፡
[115] ሮሜ 6፥23፡፡
[116] ዕብራውያን 9፥22፡፡
[117] ዕብራውያን 9፥14፡፡
[118] ዕብራውያን 10፥29፡፡

# በተባረከች ልጇ ቀኝ

መድኀኒታችን «በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው...» እንደሚያደርግ በተናገረበት ስፍራ በቀኙ በኩል የሚሆኑት በጎች «ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ...» የተዘጋጀላቸውን መንግሥት እንደሚያወርሳቸው ይናገራል፡፡[119] ለዚህም ደግሞ የሚጠበቅብን አንድና ብቸኛ ነገር በእርሱ ማመን ብቻ ነው፡፡ በዚህ መንገድ በክርስቶስ ቀኝ ለመሆን የታደለ ሰውም መጽሐፍ ቅዱስ በማያስተምረው ሰውኛ አስተሳሰብ ተስቦ ከየትኛው ፍጡር ቀኝ ለመሆን አይናፍቅም፤ አይደክምም፡፡

የድርሳኑ አዘጋጆች ግን «<u>ብፅዕት ሐናን በክብር በገናናነት የሰማይና የምድር ንግሥት በሆነች በተባረከች ልጇ ቀኝ ቁማ ባይዋት ጊዜም ሁሉም ያለቅሳሉ</u>»፡፡[120] በማለት ሐናን በማርያም ቀኝ ያስቀምጣታል፡፡ ለማልቀሳቸው ምክንያቱ ደግሞ ከዚህ ቀደም «<u>ስለናቋትና ስለገፏትም በእግዚአብሔር ዘንድ የምታሳስብ /የምታስፈርድ/</u>» ስለሆነች ነው፡፡[121]

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ስላቀለሉትና ቸል ስላሉት ብቻ ሳይሆን ከመትፋት ጀምሮ እስከ ስቅለት ድረስ (መግረፍ፣ ማንገላታት፣ ማስቃየት፣ ልብሱን መግፈፍ፣ የእሾህ አክሊል በራሱ ላይ ማድረግ፣ መራራ ነገር ማጠጣት...) ላደረሱበት ሰዎች «ይቅር በላቸው» እንጂ የፍርድ ነገር አልተናገረም፡፡[122] አሁንም ይህ ሁሉ በደል ሲከናወን ዝም ያለው ሁሉ ወደ መዳን ይደርሱ ድረስ እየታገሰ መሆኑን መመልከቱ ምን ዓይነት አፍቃሪ አባት እንዳለን ያስረዳል፡፡

የድርሳኑ አዘጋጆች ያስተዋወቋት ሐና ግን በማርያም ቀኝ ያለችው ስለ ኀጢአተኞች ልትለምንና ልትማልድ ሳይሆን፣ ለምን ናቁኝ? ለምንስ ቸል አሉኝ? በሚል ፍረድልኝ ለማለት መሆኑ ሲታይ ድርጊቷ ከሐማ ጋር የሚያመሳስላት ጨካኝ ሴት እንጂ ሩኅሩኅ አማላጅ አለመሆኗን ያረጋግጣል፡፡ ታዲያ ናቁኝ ብላ የፍርድ ያለህ እያለች ወደምትጮህ ሴት መጸለይ ፋይዳው ምንድን ነው? እንዲህ አልተከበርሁም ብላ

---

[119] ማቴዎስ 25፥33-34፡፡
[120] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘረቡዕ ቊጥር 8 ገጽ 46፡፡
[121] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘረቡዕ ቊጥር 7 ገጽ 46፡፡
[122] ሉቃስ 23፥34፡፡

አቤቱታ የምታቀርብ ሴት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመናቅም ሆነ ቸል በማለት ለሚበድሉ ሰዎች የሚማልድ ምን ዓይነት ስብዕና ይኖራታል?

## «የውዳሴና የምስጋና እጅ መንሻ» ይገባታል

ያዕቆብ ለወንድሙ ለዔሳው ካቀረበው ጀምሮ ሰብዓ ሰገል ለኢየሱስ እስካቀረቡት ድረስ የተለያዩ እጅ መንሻዎች መቅረባቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ይሁንና እነዚህ እጅ መንሻዎች ቁሳዊ እንጂ የውዳሴና የምስጋና እጅ መንሻዎች አይደሉም፡፡[123] በአንጻሩ መጽሐፍ ቅዱስ ውዳሴና ምስጋና የሚገባውን ማን እንደ ሆነ ሲያስተዋውቅ፤

- «በምስጋና የተፈራህ ድንቅን የምታደርግ»፣[124]
- «ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ ከጠላቶቼም እድናለሁ»፣[125]
- «የአምላክ ልጆች ሆይ፣ ለእግዚአብሔር አምጡ፡፡ ክብርንና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ»፣[126]

በማለት ሲሆን ውዳሴን በተመለከተ ዳግም «በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላላም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ»[127] በማለት ውዳሴም ሆነ ምስጋና የእግዚአብሔር እንደ ሆነ ያሳያል፡፡

ታዲያ የድርሳኑ አዘጋጆች የእግዚአብሔር የሆነውን ምስጋና ‹ምነው ለእርሱ ብቻ?› በሚል መንፈስ ይመስላል ለፍጡርም ለማጋራት፣ «<u>የአዶናይ (የእግዚአብሔር) እናቱ (ለእመቤታችን) እናት ለሆነች ለሐና የውዳሴና የምስጋና እጅ መነ[ን]ሻ ይገባል፡፡ የሁለተኛዋ ሰማይ መገኛ እርሷ ናት፡፡ የጸሎቷ ኃይልም የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆንን ሁላችንንም ይጠብቀን…</u>»[128] የሚል መልእክት አስተላልፈዋል፡፡ በዚህ መልእክታቸውም እንደ ተለመደው ሦስት ስሕተቶችን ሠርተዋል፤

---

123 ዘፍጥረት 32÷13፤ ማቴዎስ 2÷11፡፡
124 ዘጸአት 15÷11፡፡
125 2ኛ ሳሙኤል 22÷4፤ መዝሙረ ዳዊት 18÷3፡፡
126 መዝሙረ ዳዊት 29÷1፡፡
127 ራእይ 7÷12፡፡
128 ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘረቡእ ቍጥር 10 ገጽ 48፡፡

1. ቀደም ሲል እንደቀረበው ውዳሴም ሆነ ምስጋና የሚቀርበው ለእግዚአብሔር ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ማንነቷና ምንነቷ የማትታወቅን ሴት «የውዳሴና የምስጋና እጅ መንሻ» ይገባታል ይላል፡፡ ይህ ከቃለ እግዚአብሔር የራቀው የድርሳኑ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ጉያ ውስጥ ተሸሽጎ ቅዱስ ለመምሰል ቢሞክርም፣ እውነተኛ ሚዛን የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ አጠገቡ ሲቀመጥ ግን ጭንብሉ ወልቆ ማንነቱ ገሀድ ይወጣል፣

2. በድርሳኑ ውስጥ ሁለተኛ ሰማይ ሆና የተገለጠችው ማርያም ስትሆን ሐና ደግሞ የሁለተኛው ሰማይ መገኛ ተብላ ተጠርታለች፡፡ ማርያም ሁለተኛ ሰማይ ከሆነች የሰማዩ «መገኛ» የተባለችው ሐና ደግሞ የሰማዩ «ፈጣሪ» መሆኗ ነው ማለት ነው፤ ይህም ስሕተት ነው፡፡

3. የሐና የጸሎቷ ኃይል ሁላችንንም ይጠብቀን የሚለው የድርሳኑ መልእክት የእግዚአብሔርን ጠባቂነት አልሻም የሚል ድፍረት የተሞላበት መልእክት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያናችንን አሁን ወዳለችበት ወደ ተሳሳተው መንገድ ያስገቧት እንዲህ ያሉ ከኑፋቄ በላይ ከክህደት በታች የሆኑ ጸረ ወንጌል ትምህርቶች ናቸውና መጠንቀቅ ይገባል፡፡

## የፈጣሪን ለፍጡር

ዘማሪው «የባስ አታምጣ ከዚህ በላይ...» እንዳለው አሁን ካነበብነው በላይ ባናነብ፣ ከዚህም በላይ ባናይ ምንኛ ግሩም ነበር፡፡ ነገር ግን የክህደት ቁልቁለት ማንደርደር ከጀመረ ወስዶ ወስዶ ካልጣለ አያቆምምና የድርሳኑ አዘጋጆች ወደ ከፋው ክህደታቸው የደረሱበት ጫፍ ላይ ደርሰናል፡፡

የደርሳኑ አዘጋጆች ሐናን ሲያሻቸው ከማርያም እኩል፣ ደስ ሲላቸው ለእግዚአብሔር የሚገባውን ለሐና በመስጠት ኑፋቄአቸውን ሲዘሩ ቆይተው አሁን ደግሞ «... ፍሬዋም ለተራቡት ምግብ ነው፡፡ የደሟ እጎልም ለተጠሙት መጠጥ ነው፡፡

ለተገፉት መጠጊያቸው በኀጢአት ለተገዙትም ነጻነታቸው ናት›› በማለት ክህደታቸው የደረሰበትን ጥግ አሳይተዋል፡፡[129]

አዘጋጆቹ ምን ዓይነት ጥፋት እንደ ሠሩ አንባቢው በራሱ እንዲያስተውል ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ ይመልከት፤

| ድርሳነ ኢያቄም ወሐና | መጽሐፍ ቅዱስ |
|---|---|
| ለተራቡት ምግብ - ሐና | ‹‹ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፣ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ››[130] |
| ለተጠሙት መጠጥ - ሐና | ‹‹ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ፡- ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፣ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ››[131] |
| ለተገፉት መጠጊያ - ሐና | ‹‹እግዚአብሔርን፡- አንተ መጠጊያዬ ነህ፤ ለምን ረሳኸኝ? ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ ለምን አዝኜ እመላለሳለሁ? እለዋለሁ››[132] |
| ነጻነታችን - ሐና | ‹‹በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ››[133] |

ይህ ሰንጠረዥ እንደሚያሳየው በቅዱሱ መጽሐፍ ለፈጣሪ የተነገረው (የሆነው) ሁሉ ለፍጡር የመስጠቱ የአዘጋጆቹ ተግባር ከስሕተት በላይ የሚያስጠይቅ ድፍረት ነው፡፡

[129] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘዓርብ ቊጥር 17 ገጽ 87፡፡
[130] 1ኛ ቆሮንቶስ 10÷3-4፡፡
[131] ዮሐንስ 7÷37፤ ራእይ 22÷17፤ ኢሳይያስ 55÷1፡፡
[132] መዝሙረ ዳዊት 42÷9፡፡
[133] ገላትያ 5÷1፡፡

አንባቢው እዚህ ጋር ጠላት ምን እየሠራ እንደ ሆነ ሊያስተውልና ካለበት የእንቅልፍ ሕይወት ሊወጣ ይገባዋል፡፡

## መንግሥተ ሰማያት ለመግባት…

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ የሚቻልበትን መንገድ ያስቀመጠው «እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፣ ቤዛነቱንም እርሱንም የኀጢአትን ስርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን» በማለት ሲሆን መንግሥቱ የሚወረስበትን ሌላ አማራጭ መንገድ አላቀረበም፡፡[134]

የድርሳኑ አዘጋጆች አማራጭ ያለ መኖሩ ጉዳይ ሥጋት ላይ ሳይጥላቸው አልቀረም፡፡ ስለዚህም መፍትሔ መስሎ የታያቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግቢያ ሌላ አማራጭ መንገድ ማበጀት ነው፡፡ አማራጩንም ማርያም በተጸነሰችበት በነሐሴ ሰባት ያደርገዋል፡፡ ሐሳቡንም በሚከተለው መንገድ ያቀርባል፤ «…<u>በዚህች ዕለት የተራቆተውን የሚያለብስ፣ የተራበውን የሚያበላ፣ ያዘኑትን የሚያጽናና ብፁዕ ነው፡፡ ለታሰሩ ሰዎች የሚላላክ፣ በዚህችን ዕለት በሽተኞችን የሚጐበኝ ብፁዕ ነው በመንግሥተ ሰማይም ክፍሉ (ዋጋው) ከኢያቄምና ከሐና ከድንግል ማርያም ጋር ይሆናል</u>»[135] በማለት ለመንግሥተ ሰማያት መግቢያ ቁልፍ በነሐሴ ሰባት (ምክንያቱ የማርያም ዕለተ ጽንሰት በመሆኑ) በጐ ተግባራት የሚፈጽም ሰው ከሐና ከኢያቄምና ከልጃቸው ከማርያም ጋር በገነት መንግሥተ ሰማያት (እነሱ እዛ ናቸውና) ይገባል፡፡

በእርግጥ እንደ ተባለው እነዚህን በጐ ምግባራት ማድረግ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ ከሆነ በነሐሴ ስድስት (ዕለቱ ኢየሱስ[136] ነውና) ወይም በስምንት (ዕለቱ አባ ኪሮስ ነውና) ያደረገ ሰው ምን ምን በረከት እንደሚኖረው ያልተናገረው ለምን ይሆን?

---

[134] ቈላስይስ 1፥13-14፡፡

[135] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘእሑድ ቍጥር 7 ገጽ 102-103፡፡

[136] በርግጥ አሁን አሁን በዕለቱ ፈጣሪ የሆነውን ኢየሱስን ከማክበር ይልቅ በፍጡር አምልኮ እየተዋጠ መሆኑ በግልጽ እየታየ ነው፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት በሆነ ዕለት የሆነ ነገር በማድረግ የምትገኝ ከሆነ እንዴት በቅዱስ ቃሉ ሳይነገረን ቀረ? ይህም እስከ ሞት በሚደርስ መከራ ከተገኘው ቤዛነት ይልቅ ቀላሉ መንገድ ስለሆነ አድርጉ ብሎ መንገሩ በተሻለ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩ ብዙ ደጋግና እግዚአብሔርን የሚፈሩ አባቶችም ሰንበትን (ቀናትን) በማክበራቸው የእግዚአብሔር መንግሥት የእነርሱ በሆነች ነበር፡፡ ባጭሩ የክርስቶስ መሞት ባላስፈለገ ነበር፡፡

## ስሙን በማይጠፋ ብርሃናዊ ቀለም ይጻፈው

«የብፅዕት ሐናን ዜና የሚናገር ይህን መጽሐፍ የጻፈውን፣ የክቡር ኢያቄምን የልደቱን ዜና የጻፈውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስሙን በማይደመሰስ (በማይጠፋ) ብርሃናዊ ቀለም ይጻፈው፡፡ ጸሐፊው ተስፋ ሚካኤልንም ከማይደመሰስ የርኩሰት ኀጢአታዊ መንገድ ያድነው፡፡ የሐናና የኢያቄም አማላጅነትም በስቃይና በነቀፋ ቀን ጸሐፊውን ይጠብቅ ለዘላለሙ አሜን»[137] የሚለው ሌላው የድርሳኑ ሐሳብ ነው፡፡

የተለያዩ የገድላት፣ የድርሳናትና የተኣምራት መጻሕፍት አዘጋጆች ይህን መንገድ ይከተላሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ደግሞ መጽሐፉ ተነባቢ እንዲሆንና ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡ የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆችም «ይህን መጽሐፍ የጻፈውን» ሰው ስም በማይጠፋ ብርሃናዊ ቀለም ይጻፈው ሲሉ ይህን መጽሐፍ በመጻፍ የሰማያዊው መንግሥት ተካፋይ ለመሆን ያላቸውን ረሀብ ያሳያል፡፡ ከዚህ በመቀጠል «ጸሐፊው ተስፋ ሚካኤልንም» ከኀጢአታዊ መንገድ ያድነው ሲል ያቀረበው ሐሳብ የጸሐፊው የውስጥ ጩኸት ጽድቅ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ሁሉም ሰው ለመጽደቅ የሚፈልግና ገነት፣ መንግሥተ ሰማያትን የሚሻ በመሆኑ ተስፋ ሚካኤል ይህን መሻቱን በማስፈሩ ምንም ስሕተት አልሠራም፡፡ ስሕተቱ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማግኘት ድርሳኑን በመጻፉና የሐናና የኢያቄምን አማላጅነት በመተማመን የሚጸድቅ እንደ ሆነ ተስፋ በማድረጉ ነው፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ «የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው»[138] እና «ነገር ግን የሚመካ

---

[137] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘእሑድ ቍጥር 10 ገጽ 104-105፡፡
[138] ሮሜ 8፥33፡፡

በእግዚአብሔር ይመካ፣ ተብሎ እንደ ተጻፈው ይሆን ዘንድ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ የሆናችሁ በእርሱ ነው»[139] በማለት ጽድቅ የሰዎችን ታሪክ በመጻፍና በፍጡራን ምልጃ እንደማይገኝ ያስረዳልና፡፡

መጽሐፍ መጻፍ ኀጢአት ያልሆነ በጎ ተግባር ቢሆንም ለጽድቅ የሚሰጠው ዋጋ ግን የለም!!! ሰዎች መጽሐፍ በመጻፋቸው የሚጸድቁ ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የመዳን ዋስትና ባገኙ ነበር፡፡ ነገር ግን እነርሱ ያሰፈሩት የሚከተለውን ነበር፤ «ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን፣ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፣ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል»፡፡[140] ስለዚህ ከዚህ ውጪ በሆነ መንገድ እንጸድቃለን የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ «የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም» ተብሎ እንደ ተጻፈው መሆናቸው ነው፡፡[141]

## የአዳም መድኀኒት «ሐና»?

«አዳኝ፤ በሥጋም ሆነ በመንፈስ ከማናቸውም ክፉትና ጉዳት የሚያድን ወይም የሚጠብቅ መድኀኒት አዳኝ ታዳጊ ይባላል»፡፡[142] በመጽሐፍ ቅዱስ አዳኝ፣ ታዳጊ የተባሉ የተለያዩ ሰዎች ቢኖሩም አንዳቸውም ግን ከኀጢአት ጋር በተያያዘ አዳኝ፣ ታዳጊ ወይም መድኀኒት ተብለው አያውቁም፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው አዳኝ ወይም ታዳጊ የተባሉት ሰዎች «አዳኝ» የተባሉት በጊዜው አጠገባቸው የነበሩትን ሰዎች በጊዜው ከመጣቸው ጊዜያዊ ችግር ስላዳኗቸው መሆኑን ከገጸ ንባባቸው እንረዳለን፡፡

የድርሳኑ አዘጋጆች፣ «ላዘነ ለአዳም መድኀኒቱ ለተገደለ ለአቤልም የቤቱ መሠረት የሆንሽ እመቤቴ ሐና ሆይ ለአንቺ የምሥራች ይገባሻል፡፡...» በማለት ለአዳም

---

[139] 1ቆሮ. 1፥30-31፡፡
[140] ገላትያ 2፥16፡፡
[141] ሮሜ 10፥3፡፡
[142] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (ዐዲስ አበባ፣ 1998 - ስምንተኛ ዕትም) ገጽ 44፡፡

መድኀኒቱ ነሽ ሲሏት ከኀጢአት ጋር አያይዞ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡[143] አዳም በዘመነ ሐና በአካል የሌለ መሆኑና ሐና የአዳም መድኀኒት መሆኗ ለየትኛው ችግሩ እንደ ሆነ አለመገለጹ መድኀኒትነቷ በመንፈስ መሆኑን ያሳያልና፡፡ ትዳር ሳይዝ ኀጃ ሳይሠራ ለሞተውና በዘመነ ሐና ላልነበረው ለአቤል የቤቱ መሠረት ነሽ የተባለችው ሐና በመንፈስ ካልሆነ ከቶ በምን ሊሆን ይችላል?

ለኀጢአት «መድኀኒት» ስለሆነው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱሱ መጽሐፍ በተደጋጋሚ የተጻፈ ሲሆን ከፍጡራን መካከል ግን «የኀጢአት መድኀኒት» ለመሆን የሚችል ስለ መኖሩ የሚሰጠው ፍንጭ እንኳ የለም፡፡[144] ድርሳኑ የሚያስተምረውን እንግዳ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን አሾልኮ ማስገባት ልማዱ የሆነው ጠላታችን ይህንም እንደ እውነተኛ ትምህርት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለማስገባት የተጠቀመባቸው የድርሳኑ አዘጋጆችና አሳታሚዎች ለሠሩት ለዚህ በደል ንስሐ ሊገቡ ይገባቸዋል፤ ቤተ ክርስቲያንም ኑፋቄውን ማውገዝና ለምእመናን ማሳወቅ ይጠበቅባታል፡፡

## እስከ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም የሚመሰገን ስም

ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን ማመስገን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡ ስለዚህ እርሱ የዓለማት መጋቢ፣ የፍጥረት ሁሉ አባት፣ የኀጢአት ሁሉ መድኀኒት … በመሆኑ መመስገን ገንዘቡና ተገቢው ነው፡፡ ታዲያ ይህ ባሕርይና ሥልጣን ለሌላቸው ፍጡራን ምስጋና የምናቀርብበት ምክንያት ምን ይሆን?

- እነርሱ ፈጣሪዎቻችን ናቸውን?
- እነርሱ መጋቢዎቻችን ናቸውን?
- እነርሱ የዓለማት አስተዳዳሪዎቸ ናቸውን?
- እነርሱ ለጸሎታችን መልስ የሚሰጡ ናቸውን?
- እነርሱ ለኀጢአታችን ስርየት የሚሆን ነገር ያቀረቡ ናቸውን?

[143] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘረቡእ ቍጥር ፲ ገጽ 48፡፡

[144] ሉቃስ 2፥11፤ ዮሐንስ 4፥42፤ የሐዋርያት ሥራ 5፥31፤ ፊልጵስዩስ 3፥20፤ ፩ኛ ዮሐንስ 4፥14፡፡

ለዚህ ሁሉ ጥያቄ የሚኖረው መልስ፣ «አይደሉም» የሚል ከሆነ ምስጋናችንን ለእነርሱ የምንቸረው ለምንድን ነው? ደግሞስ ለፍጡራን ምስጋናዎቻችንን ስናቀርብ ፈጣሪን በየትኛው ጊዜያችን ልናመሰግን ይሆን?[145]

ለዚህ ሐሳብ መነሣት ምክንያት የሆነው «...ስምህም እስከ ዓለም ፍጻሜ ከላይ ከጽርሐ አርያም የምትወርድ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም እስከምትባል ድረስ ይመሰገናል» በማለት ለኢያቄም ያቀረበው ያልተገባ የምስጋና መስዋዕት ነው፡፡[146]

ይህን እና ይህን መሰል የኑፋቄ መምህራን እስካሉና ይህን መሰል የኑፋቄ ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባታቸው እስካልቀረ (የገቡትም እስካልተወገዱ) ድረስ እግዚአብሔርን ማሳዘናችንን እንቀጥላለን፡፡ የእግዚአብሔር የኀዘን ጽዋ ስትሞላ ደግሞ ምድራችንን ለክፉው አሳልፎ እንዳይሰጥ ያሰጋል፡፡

## ትንቢተ ሐና

እግዚአብሔር የተለያዩ ነቢያትን አስነሥቶ የተደረገውን፣ እየሆነ ያለውንና ወደፊት የሚሆነውን በማናገር ሕዝቡን ሲያስጠነቀቅ፣ ሲመክርና ሲገስጽ ኖሯል፤ አሁንም ከቅዱስ ቃሉ በመነሣት እየመከረና እየገሰጸ፣ እያስጠነቀቀና እያሳሰበ ይገኛል፡፡

እንደ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች እምነት የብሉይ ኪዳን ሴት የሆነችው ሐና ለመዳን የምትሆን አማራጭ፣ ምስጋና የሚገባት፣ ጸሎትን የምትሰማ ብቻ ሳትሆን ነቢይትም ናት፡፡ የትንቢት ቃሏም እነሆ፤

...ሐና በቤቷ ሳለች በልቧ አሰበች፡፡ ስለ ልጇም ስለ ልጄ ምን ላድረግ? ይህ ነገር እውነት ከሆነ አምላክ በእርሷ ማኅፀን

---

[145] በየአዋልድ መጻሕፍቱ የተጻፉትን ብንመረምር ሁሉም ቅዱስ ምስጋና የሚገባው መሆኑን መመልከት እንችላለን፡፡ «እስከ አሁን ባገኘናቸው መረጃዎች መሠረት ኢትዮጵያውያን ቅዱሳን ቁጥራቸው ከሦስት መቶ ይበልጣል» የሚለው ዳንኤል ክብረት ከ200 በላይ ገድላት መታተማቸውን ይነግረናል (ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን)፣ ኢትዮጵያዊው ሱራፌ (ኅዳር 2011) ገጽ 67-68)፡፡ ሦስት መቶ ይበልጣሉ የተባሉትን ቅዱሳን ተከትለን ሳይሆን ገድላቱን ብቻ መሠረት በማድረግ ድርሳናትና ተኣምራትን ጨምረን ምስጋና የሚገባቸውን ፍጡራን ቁጥር ስንመለከት በርግጥም በየትኛው ጊዜያችን ጌታችንን እናመሰግን ይሆን?

[146] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘዓርብ ቁጥር 19 ገጽ 87፡፡

> ካደረና ከተፀነሰ የእስራኤል ሕዝቦች ሁሉ ስለሚቀኑ እንዴት ያደርጓት ይሆን? እውነተኛ የሆነ የልጇ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ድምፅ በሰሙ ጊዜ እርሷን አገር ለአገር ያንከራትቷል፡፡ ልጇንም ከኢየሩሳሌም ውጪ ይሰቅሉታል፡፡ ስለ ልጄ ምን ላድርግ? ለእኔ አንዲት ናትና፣ እኅትም ወንድምም የላትምና ያስጨንቀኛል፡፡ ስለ እርሷም አዝናለሁ፡፡ በእርሷ የሚፈጸመውን የእስራኤልን ተግዳሮትም አስባለሁ፡፡ በኋላ ግን ለምድር ሕዝቦች ሁሉ ሰላምን፣ ይቅርታንና ቅንነትን ታፈራለች፡፡[147]

‹ስለ ልጄ እፈራለሁ› የምትለው ሐና ይህ ሁሉ ፍራቻና ጭንቀት የሆነባት የማርያምንና የኢየሱስን ሁኔታ መነሻ አድርጋ ነው፡፡ ቀደም ብላ ስለ ማርያም «…ሰማይና ምድር የሰውና የመላእክት ፍጥረት ሁሉ የልጄን አንዲት የራስ ፀጉሯን ዋጋ አይሆኑም»[148] ያለችውን የዘነጋችው «ነቢይት» ሐና አሁን ደግሞ «ስለ እርሷም እጨነቃለሁ» ትላለች፡፡

ፍራቻዋና ጭንቀቷ ማርያም ኢየሱስን ከመውለዷ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሐና ቅድመ ክርስቶስ የነበረችና በአዋልድ መጻሕፍት ምስክርነት መሠረት ማርያምም ኢየሱስን በ15 ዓመቷ ስለ ወለደችው፣ ከኢየሱስ ልደት ከ15 ዓመት በፊት የተናገረችው ትንቢት ሲሆን በብሉይ ኪዳን ዘመን (ቅድመ ልደተ ክርስቶስ) አገልግሎት ላይ ያልዋሉ፤

1. አምላክ እንደሚወለድ፤ «አምላክም በእርሷ ማኅፀን ካደረና ከተፀነሰ»
2. ይህ የሚለወደው ኢየሱስ እንደሚባል፤ «የልጇ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን…»
3. ከኢየሩሳሌም ውጭ እንደሚሰቀል፤ «ከኢየሩሳሌም ውጪ ይሰቅሉታል…»

---

[147] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሡሉስ ቍጥር 17 ገጽ 38-39፡፡

[148] ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ድርሳነ ኢያቄም ወሐና - በግእዝ እና በአማርኛ (2007) ዘሡሉስ ቍጥር 4 ገጽ 28፡፡

የሚሉትን በመጥቀስ «ትንቢት» መናገሯ እንዴት ነው ነገሩ? ይህን የተናገረችው ይህቺ ሴት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ነው ወይስ ድኅረ ልደተ ክርስቶስ? የሚል ጥያቄ ማስነሣቱ አይቀርም፡፡

ከዚህም ሌላ በእርሷ አባባል ማርያም በመጨረሻ «ለምድር ሕዝቦች ሁሉ ሰላምን ይቅርታንና ቅንነትን» የምታፈራ ከሆነ ስለ እርሷ መፍራትና መጨነቁ ስለምን ይሆን? ደግሞስ ሰላምና ይቅርታን የምታፈራው ማርያም ናትን? የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ነውን የሚያስተምረው? እንድንል ያስገድደናል፡፡

# ማጠቃለያ

ሰዎች ስሜታቸውንና ልማዳቸውን ተከትለው የሚያደርጉት ነገር ከቃለ እግዚአብሔር የሚያርቃቸውና ወደ ተሳሳተ መንገድ የሚወስዳቸው ከሆነ አካሄዳቸውን በመመርመር ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመመለስ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

የድርሳነ ኢያቄም ወሐና አዘጋጆች (ተርጓሚ አርታዒና አሳታሚ) ከዚህም በፊት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንግዳ ትምህርቶችን አሾልከው ያስገቡና እውነተኛ ትምህርት መስሎ ቦታ እንዲይዝ ያደረጉ ልማደኞች ናቸው፡፡ ይህ አካሄዳቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ በተለያዩ ወንድሞችና አባቶች በተለያዩ መንገዶች የተገለጸ ቢሆንም ከቀድሞ ስሕተታቸው ከመታረምና ወደ ትክክለኛው መንገድ ከመምጣት ይልቅ በጥፋት ላይ ጥፋትን መጨመርን ነው የተያያዙት፡፡ ለዚህም ቀደም ሲል ፍተሻ የተደረገበት መጽሐፍ (ድርሳነ ኢያቄም ወሐና) ጥሩ ማሳያ ነው፡፡

በድርሳኑ የዘሯቸው የኑፋቄ ዘሮች እንደሚያሳዩት ከሆነ አዘጋጆቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር ክፉኛ እየተጋጩ ነው፡፡ ይህን የሚያደርጉትም ተሳስተው ሳይሆን አስበውበት መሆኑን መጽሐፋቸው ያረጋግጣል፡፡

የሚገርመው የእነርሱ በጥፋት ላይ ጥፋት መደራረብ ሳይሆን መንጋውን በአደራ የተረከቡት እረኞች (አባቶች) ድምጽ መጥፋት ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ማንም እየተነሣ ከየት እንዳመጣው እንኳ የማይታወቅ የስሕተት ትምህርት ሲያራግፍባት እንዲህ ያለ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የለም፤ ይህ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት አይደለም የሚልና መጥፎውን ከጥሩው ለይቶ የሚያሳይ አባት ያስፈልግ ነበር፡፡

እንደዚህ ያሉ አባቶች አለመኖራቸው ለጥንተ ጠላታችን ለሰይጣንና ለታማኝ ደቀ መዛሙርቱ ስለ ተመቻቸው ያለ ከልካይ የወደዱትን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ የተነሣ እረኛ መሆን የሚችሉ አባቶች እስከሚነሡና በጐቹን መጠበቅ እስከሚጀምሩ ድረስ ፍሬውን ከገለባው ለይቶ በማሳየት ምእመናን ፍሬውን እየተጠቀሙ ገለባውን ለነፋስ እንዲሰጡት በዚህ መልኩ ጥሪ ማስተላለፋችን እንቀጥላለን፡፡

በነገር ሁሉ የረዳን አምላክ ለቤተ ክርስቲያናችን የሚያስቡና የሚጋደሉ አባቶች በማስነሣት የተሻለውን ዘመን እንዲያመጣልን ጸሎታችን ነው! አሜን!!!

**እግዚአብሔር ቢፈቅድ በቅጽ - ፪ ድርሳነ ማርያም የተሰኘውን መጽሐፍ እንመለከታለን፡፡**

